# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔ[1]

ሊያ መዝገቡ*

## Abstract

Human being has social process which could enable him/her to transform from one mode of experience to the next. The process of transforming from one cumulative experience to the next transformed experience could reflect all the process, successes, challenges, merits and demerits of certain group of entities. In line with this, the Ethiopian Orthodox Tewahido Church has developed rich and prominent mode of holy orders which could enable one religious person to promote from the lower hierarchical order to the next. This transition is known as Rite of Passage. Here, a clergy or a candidate for the next hierarchical order will get the chance of advancement to a higher class or a new appointment for more religious services. This process could be affected by the religious or social practices accumulated through a long period of time. Thus, having this in mind the researcher questioned "What the holy order of the Ethiopian Orthodox Tewahido Church considers during ordination?" The researcher also tried to answer this basic question by interviewing church scholars, reviewing different existing written documents and physical observation as well.

The main objective of the research is to come up with evidence why, how, when, where, and what criteria is needed for the advancement to a higher class in the Church's hierarchy, who is the potential candidate/illegible for such holy order. By doing so this study also tries to answer the change/experience/ that a person who undergo the holy order and come up to the next hierarchical order is exhibiting.

The hierarchical holy order of the Ethiopian Orthodox Tewahido Church entitles the candidate to become more acquainted with the church's religious principles and be able to serve God and the religious community.

---

*ሊያ መዝገቡ በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የዐማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል መምህርት ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ በዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሦስተኛ ዲግሪያቸውን (ዶክትሬት) በመማር ላይ ናቸው።

[1]ይኽ ጽሑፍ በ፳፻፫ ዐ.ም. ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና የባህል ጥናት (ፎክሎር) ትምህርት ክፍል ‹‹በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርቲያን የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔ›› በሚል ርእስ ለኹለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ከቀረበው የጥናት ጽሑፍ ላይ ለዚኽ የጥናት መጽሔት አመቺ እንዲኾን ተደርጎ የቀረበ ነው፡፡

## ፩. መግቢያ

ሹመት (advancement to a higher class) አንድ ግለሰብ ወግ መዓርጉን ከሚያይባቸው ገጽታዎች መካከል አንዱ ነው። አንድ ሰው ወግ መዓርጉን ሲያይ ማኅበረሰቡ አሜን ብሎ የሚቀበለው ለዚህ ሰው የተለያዩ ሥርዐተ ክዋኔዎች ሲፈጸሙለት ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን የተባሉት ሦስቱ መዓርጋት ማለትም ዲቁና፣ ቅስና እና ኤጲስ ቆጶስነት ሲሰጡ የሚከወን ሥርዐተ ሢመት አለ። በመኾኑም የዚኽ ጽሑፍ ዋና ትኩረት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔን መመርመር ሲኾን ለምርምሩ መነሻ የኾኑ ጥያቄዎች የመነጩት ከክህነት ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ፋይዳ አንጻር በሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔ ላይ የሚፈጸሙ ኹነቶችን ጠንቅቆ ለማወቅ ሲባል ነው። የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዐት እንዴት? መቼና የት? በማንስ ይካሔዳል? የሥልጣነ ክህነት ዐይነቶችስ ምን ምን ናቸው? የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔ ለምን ይጠቅማል? ሥልጣነ ክህነትን ለማግኘት መፈጸም ያለባቸው ቅድመ ኹኔታዎች ምን ምን ናቸው? በሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔ ላይ የሚፈጸሙ ድርጊቶች ወይም ክዋኔዎች ምን ምን ናቸው? ክዋኔው የሚኖረው ፎክሎራዊ[2]ገጽታስ ምንድነው? የክዋኔዎች ትእምርታዊ[3] ፋይዳስ ምንድነው? ሥልጣነ ክህነትን የተቀበሉ ግለሰቦች የአለባበስ ሥርዐትና የአኗኗር ልማድ ከሌላው ማኅበረሰብ ለምን ተለየ? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅና ለጥያቄዎቹም መልስ በመሻት ነው። ከጥያቄዎቹም በመነሣት የሚከተሉት ነጥቦች የጥናቱ ዐላማዎችም የሥርዐተ ክዋኔው አፈጻጸም መነሻ ከየት እንደኾነና ለምን እንደሚፈጸም፣ ሥልጣነ ክህነትን የሚቀበሉ ግለሰቦች ማሟላት የሚጠበቅባቸው መሥፈርቶች ምን ምን እንደኾኑ፣ ሥርዐተ ክዋኔው ለየትኞቹ የሥልጣን ዐይነቶች እንደሚፈጸም፣ በሥርዐተ ክዋኔው ምን? ለምን? በማን? እንዴት? የት? እና መቼ? እንደሚፈጸም፣ ሥርዐተ ክዋኔው በተፈጸመላቸው ሰዎች ላይ የሚያድርባቸውን ጸጋ፣ የሚታየውን የሕይወት ለውጥ እንዲሁም ግለሰቦቹ በተለያዩ ማኅበረሰቦች ውስጥ የሚሰጡትን መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ እና ግለሰባዊ አገልግሎት (ፋይዳ) መጠቆምና መግለጽ ናቸው።

እነዚህን ዐላማዎች ለማሳካት በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በሠነድ ምርመራና በቡድን ውይይት መረጃዎች ተሰብስበዋል። ክዋኔውን ለመተንተንና ለመተርጐም

---

[2] ፎክሎር (የባህል ጥናት) የተለያዩ ብያኔዎች አሉት። በጥቅሉ የአንድን ማኅበረሰብ ዕውቀት፣ እምነት፣ ልማድ፣ ዕሴት፣ አመለካከት፣ ግንዛቤና ስሜት የሚገልጥ ስለ ሰዎች ማንነትና ስለምንኖርበት ዐለም ትርጓሜ ለመስጠት የሚያስችል ነው በማለት ሲምስና ስቴፈን ይገልጻሉ። Martha, Sims and Stephen, Martin. Living Folklore: An Introdroduction to the Study of Peple and their Tradition. (Ohio: Utah State University Press, 2005).

[3] ምልክት ማለት ነው።

ይቻል ዘንድ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ የመንፈሳዊ ኮሌጆችና ትምህርት ቤቶች መምህራንና የተለያዩ ምእመናን ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል። እንዲሁም ዲቁናን ከተቀበሉ ስድስት ዲያቆናት ጋር የቡድን ውይይት በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በሠነድ ምርመራውም በኩል በቤተ መጻሕፍት የሚገኙ የተለያዩ የሥርዐት መጻሕፍትና የጥናት ሥራዎች የተዳሠሡ ሲኾን ይኽ ጥናት በሚዘጋጅበት ወቅት የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን እየተሰጠ ያልነበረ በመኾኑ (ጎልድስቲን (1964፡83)[4] አንድ አጥኚ የፎክሎር ምርምር ሲያደርግ ሥርዐተ ክዋኔው በወቅቱ የማይገኝና ዘግይቶ የሚከወን ከኾነ ከዚህ ቀደም የተጠናቀሩ መረጃዎችን በመመርመር ጥናቱን ማሟላት እንደሚችል በገለጸው መሠረት) በቪዲዮ ተቀርጾና ተሰንዶ የተቀመጠ መረጃ ለጥናቱ በምንጭነት አገልግሏል።

መረጃዎች በምልከታ ሲሰበሰቡ በዐዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሦስት አብያተ ክርስቲያናት ተመርጠዋል። የመጀመርያው ደብረ ብሥራት (ብሥራተ) ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ለክርስትና አነሣሥ ሥርዐት፣ ኹለተኛው ታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም የክህነትን ትምህርት አሰጣጥና የሚማሩትን የትምህርት ዐይነት ለማየት ሦስተኛው ደግሞ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም የዲቁና ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔን ለመመልከት አጥኚዋ በቦታው ተገኝታለች። እነዚኽ ቦታዎች የተመረጡበት ምክንያት አጥኚዋ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስትነሣ መረጃዎቹ በተጠቀሱት ቦታዎች የሚገኙ በመኾናቸው፣ በተለይ ደግሞ በወቅቱ የዲቁና ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐት በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ይሰጥ ስለነበረ ነው።

የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዐት በክዋኔ ላይ ትኩረት የሚያደርግ በመኾኑም ጥናቱ የክዋኔ (performance) ንድፈ ሐሳብ ይከተላል። ይህንን ንድፈ ሐሳብ ከቀረጹት ውስጥ ሪቻርድ ቦውማን (1983) እና ዳን ቤን አሞጽ (1982) ይገኙበታል።[5] ይኽ ንድፈ ሐሳብ ተቀርጾ ስያሜውን ከማግኘቱ በፊት ዐውዳዊ (contextual) ንድፈ ሐሳብ ይባል ነበር። ዐውዳዊ ንድፈ ሐሳብ እያደገ ሲመጣ ክዋኔ (performance) ንድፈ ሐሳብ ተብሏል። የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ በውስጡ ባህላዊና ማኅበራዊ ዐውዶችን የያዘ ነው። እነዚኽ ዐውዶች ትእምርታዊ ፍቺዎችን፣ ባህላዊ ተቋሞችንና ማኅበራዊ ግንኙነቶችን የሚያሳዩ ናቸው።

---

[4] Goldstien, Kenneth S. A Guide for Field Workers in Folklore. (London: Herbvert Jenkins, 1964), p. 83.

[5] Dan Ben Amos, “Context” in context, Journal of American Folklore, (Vol.52, No 2/4.9, 1993), P. 209-226.

የአንድ ማኅበረሰብ ባህል መኖሩ የሚታወቀው ሲከወን (perform) ሲደረግ ብቻ ነው፡፡ ክዋኔ በሕግ የሚመራ፣ የማኅበረሰብን ልማድ የሚያሳይና ትውፊት እንዲቀጥል የሚያደርግ ነው፡፡ ህልውናው የተመሠረተውም በአንድ ማኅበረሰብ ትውፊት ወይም ባህል ላይ ሲኾን የሚቀርበውም በድርጊትና በገለጻ ነው፡፡ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ጉዳዮች ተፈጻሚነት ኖሯቸው በቅደም ተከተልና በድግግሞሽ መከወን ሲችሉ ሥርዐት ይባላሉ፡፡ ሥርዐቶች የማኅበረሰቦችን ደንብ፣ መመሪያ፣ ትውፊት፣ ባህልና ሌሎችንም ጉዳዮች ገልጸው የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚኽን የአንድ ማኅበረሰብ መገለጫ የኾኑ ዕሴቶች ገልጾ ለማሳየት ክዋኔ መሠረታዊ እና ቁልፍ የኾነ መሣሪያ ነው፡፡ ይኽ ንድፈ ሐሳብ በውስጡ በክዋኔ ጊዜ ሊኖሩ የሚችሉ ባህላዊ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ትእምርቶችን የመተርጐሚያ መንገድ የኾኑ ንድፈ ሐሳቦችንም ያካተተ ነው፡፡ እነርሱም ተግባራዊ (functional)፣ መዋቅራዊ (structural) እና ትርጉማዊ (interpritative) ናቸው። ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ባህል ማኅበራዊ አገልግሎትን ይሰጣል፤ በባህል ውስጥ ለማኅበረሰቡ የማይጠቅምና ዋጋ የሌለው ነገር የለም የሚል ሐሳብ አለው፡፡ መዋቅራዊው ንድፈ ሐሳብ በራድክሊፍ ብራውን (1952)[6] የተቀረጸ ሲኾን ዋና ሐሳቡም የአንድ ማኅበረሰብ ሥርዐት ከሌሎች የእምነትና የባህል ዐይነቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ወይም ተዛምዶና ቅንጅት መመልከትና ያለውን ፋይዳ ማመልከት ነው፡፡ የትርጉማዊ ንድፈ ሐሳብ በክሊፎርድ ጊርቲዝ (1973) የተቀረጸ ሲኾን ይዞት የተነሣው ዐላማ የአንድ ማኅበረሰብ ዕሴት፣ ሥርዐትና የአኗኗር ደንብ በተምሳሌት የተበጁ ናቸውና መተርጐም አለባቸው የሚል ነው፡፡

መረጃዎቹ ከላይ በቀረቡት የመተንተኛ መንገዶች ተተንትነው ሲደራጁ አንባቢዎች መሠረታዊ ነገሮችን እንዲይዙ ለእያንዳንዱ የሥልጣን ዐይነት ሦስት ዐበይት ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡ የመጀመርያው ቅድመ ሥርዐተ ክዋኔ ነው፡፡ ይኽም ክህነትን ለመቀበል መሟላት ያለባቸውን መሥፈርቶች ይዟል፡፡ ኹለተኛው ክህነቱን ለመቀበል የሚከወነውን ሥርዐት የሚያሳይ (transition rite) ሲኾን ሦስተኛው ክፍል ደግሞ ድኅረ ሥርዐተ ክዋኔ ነው፡፡ ይኽም ካህናት በሹመታቸው የተሰጣቸውን ሓላፊነት የሚወጡበትና ከማኅበረሰቡ የተለየ የአኗኗር ዘይቤ የሚያሳዩበት ነው፡፡

[6] Brown, Radcliffe A.R. Structure and Function in Primitive Society. (Great Britain at the University press: 1952).

## ፪÷ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ

### ፪.፩. ወግ መዓርግ (Rite of Passage)

መዓርግ የአንድን ግለሰብ ሥልጣን፣ የሥራ ደረጃ፣ ከተራው ማኅበረሰብ ወይም ከወል የአኗኗር ሥልትና ዘይቤ የሚለይ ነው። መዓርግ ለሚለው ቃል ደስታ ተክለ ወልድ (1962፡954)[7] በሀብት፣ በሹመትና በመንፈሳዊ ሥራ የወጣኒ[8]፣ የማዕከላዊና የፍጹም ደረጃና ክብር የሚል ፍቺ ያቀረቡ ሲኾን የሹመትን ፍቺ ደግሞ ክብር፣ መዓርግ፣ መብት፣ የበላይነት በማለት ገልጸዋል።

የሰው ልጅ ሕይወት ተከታታይነት ባላቸው ሽግግሮች ውስጥ ያልፋል እንጂ ሁልጊዜ በአንድ የሕይወት ዑደት ውስጥ ብቻ አይሽከረከርም። እነዚህ ሽግግሮች ከአንድ የዕድሜ እርከን ወደ ሌላው የዕድሜ ክልል ወይም ከአንድ ማኅበራዊ ቦታ ወደ ሌላው የሚያስተላልፉ ናቸው። ጌኔፕ የተባለው ጸሐፊ በወግ መዓርግ ውስጥ የሚካተቱ የተለያዩ ገጽታዎችን ዘርዝሮ ከእነዚኽም ውስጥ ሹመት (advancement to a higher class) አንዱ መኾኑን በሚከተለው ሐሳብ ያስረዳል።

> Transition from group to group and from one social situation to the next one looked on as implicit in the very fact of existence, so that a man's life comes to be made up of beginnings: birth, social puberty, marriage, fatherhood, advancement to a higher class, occupational specialization, and death. For every one of these events there are ceremonies whose essential purpose is to enable the individual to pass from one defined position to another which is equally well defined (1960:3).[9]

ወግ መዓርግ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የአንድን ግለሰብ የዕድሜ ልክ ገጽታ የሚያመጣውን ለውጥና ሰዎች በአኗኗር ዘይቤያቸው ውስጥ ያሉበትን ደረጃ ወይም ሽግግር የሚያመለክት ነው። የወግ መዓርግ ገጽታዎችን የሚያሳዩ ኹኔታዎች በሦስት ደረጃዎች ተከፍለው ይታያሉ። ጌኔፕ (1960፣11) እነዚኽን ደረጃዎችመለየት (separation)[10] ሽግግር (transition)[11] እና መመለስ

[7] ደስታ ተክለ ወልድ። ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት። (ዐዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፷፪)።

[8]ወጣኒ የሚለውን ቃል ደስታ ተክለ ወልድ ጀማሪ ሲሉ ይፈቱታል (1962፣ 427)።

[9]Gennep, Arnold Van. The Rites of Passage. (Chicago USA: The University of Chicago press, 1960).

[10]መለየት (separation) የተለያዩ ግለሰቦች ሥልጣነ ክህነትን ለመቀበል ከማኅበረሰቡ ተለይተው በመውጣት ለክህነት የሚያበቁ መስፈርቶችን የሚያሟሉበት ደረጃ ነው።

[11]ሽግግር (transition) ደግሞ ከማኅበረሰቡ ተለይተው ለክህነት የሚያበቋቸውን መስፈርቶች ካሟሉ በኋላ ከነበሩበት ደረጃ ከፍ ወዳለው የሚሸጋገሩበት ነው። ይህንን አስመልክቶ የሚፈፀመው ሥርዓት ሥልጣነ ክህነት የሚቀበሉበት የክዋኔ ሥርዓት ነው።

(reincorporation)[12] በማለት የገለጻቸው ሲኾን እያንዳንዳቸው የሰው ልጅ ለወግ መዓርግ ለመብቃት የሚያልፍባቸውን የሕይወት ገጽታዎች በሒደት የሚያሳዩ ናቸው።

መዓርግ አንድ ግለሰብ ያለፈበትን ደረጃ ወይም ያለበትን ቦታና ኹኔታ የሚያመለክት ነው። አንድ ግለሰብ ለአንድ የተወሰነ ሥራ ታጭቶ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ለዚያ ሥራ ብቁ ኾኖ መቅረቡን ለማሳየት ሥርዐት ወይም ክብረ በዐል ይዘጋጅለታል። ሥርዐቱ ያንን ግለሰብ ከነበረበት ሕይወት ወይም የሥራ ድርሻ ወደ ተሻለው ወይም ከፍ ወዳለው መሸጋገሩን የሚያረጋግጥ ነው። የሽግግር ሥርዐቱ ተፈጽሞ፣ ለትልቅ ዐላማና ተግባር ወደ ቀጣዩ ክፍል ሲራመድ “ለወግ መዓርግ በቃ” ይባላል። ለመዓርግ መብቃት ሰዎች ከአንድ ቦታ ከፍ ወዳለው የሚሸጋገሩበት፣ የቀደመውን የአኗኗርም ኾነ የአስተሳሰብ ፍልስፍና ቀይረው ወይም አሻሽለው በዐዲስ አቅጣጫ የሚጓዙበት፣ ቀደም ከነበረው ሓላፊነት ከፍ ወዳለው ደረጃ የሚደርሱበት ወይም ከፍ ያለ የሥራ ድርሻን የሚወጡበት እንዲሁም የማሠልጠን፣ የማዘዝና የመምራት ብቃታቸውን የሚያሳዩበት ዕድል ነው።

## ፪÷፪÷ የሥርዐት ምንነት እና አስፈላጊነት

### ፪.፪.፩. የሥርዐት ምንነት

ሥርዐተ ክዋኔ ሽግግር (transition) የሚደረግበት ክፍል ነው። ሥርዐት “ሠርዐ” ከሚል የግእዝ ቃል የተገኘ ሲኾን ትርጒሙም የሕግና የትእዛዝ መጠበቂያ ደንብ፣ መመሪያ፣ ገደብ፣ አሠራር፣ መርሐ ግብር መኾኑን ደስታ ተክለ ወልድ (፲፱፻፷፪:፲፻፺፬ ) ገልጸዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ (ምሳ ፴÷፳፯፣ ፩ኛ ቆሮ ፲፬÷፵) እና ገላ ፩÷፲፬) ያሉትን ጥቅሶች መሠረት በማድረግ የሥርዐትን ምንነት “የመንግሥት፣ የቤተ ክርስቲያን፣ የሕዝብ ወይም የአንድ ድርጅት የአስተዳደር፣ የአመራር ወይም የአካሄድ ሕግ፣ ደንብ፣ ብያኔ” በማለት ይገልጻል።[13]

<u>ሥርዐት “ritua</u>l” የሚለውን ቃል የሚተካ ሲኾን ብዙዎቹ የፎክሎር (የባህል

[12] መመለስ (reincorporation) ሥልጣነ ክህነቱን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ማኅበረሰቡ ተመልሰው በመምጣት ተልዕኳቸውን የሚፈጽሙበት፣ የክህነት ሥልጣን መቀበላቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተለያዩ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን የሚከውኑበት ደረጃ ነው።

[13] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት። (ዐዲስ አበባ፡ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፺፪)።

ጥናት) ተመራማሪዎች የአንድን ነገር ቅደም ተከተላዊ ሂደት መመሪያ የሚያሳይ መኾኑን አመልክተዋል። የሥርዐት ህልውና የተመሠረተው በክዋኔ (performance) ላይ መኾኑን "If there is no performance, there is no ritual" "ክዋኔ ከሌለ ሥርዐት የለም" በማለት ራፖርት (1992፣250) አስረድቷል።[14]
እንዲሁም ሥርዐት አንድ ነገር ከሌላው ጋር ያለውን ተያያዥነት እና ግንኙነት የሚያሳዩ በርካታ ገጽታዎች ያሉት፣ የነገሮችን ቅንጅት ወይም መዋቅር የሚያሳይ ቅርጽ መሆኑንም ጠቁሟል። ሥርዐት የአንድን ማኅበረሰብ እምነት መሠረት ያደረጉ ሚቶች፣ አፈ ታሪኮችና ነገረ ተፈጥሮዎች የሚገለጹበት ነው። ሥርዐት ከባህል መገለጫዎች አንዱ የሆነ እና ትእምርታዊ ፋይዳ ባላቸው በልማዳዊ ድርጊቶች፣ በድግግሞሽ፣ በንግግር፣ በገለጻ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ እና በዚህም የማኅበረሰቡን አጠቃላይ ገጽታ ለማሳየት የሚያስችል ነው።[15]

## ፪.፪.፪. የሥርዐት አስፈላጊነት

ሥርዐት የተለያዩ ፋይዳዎችን ስለሚያስገኝ ማኅበረሰቦች በእምነታቸው፣ በአመለካከታቸውና በዕውቀታቸው ላይ ተመሥርተው ሥርዐት ያበጃሉ። ሥርዐት ካሉት ፋይዳዎች መካከል ከዝቅተኛ የማኅበረሰብ አባልነት ወደተሻለው፣ ከዝቅተኛ የሥራ ቦታ ወይም ከነበረ ክብርና መዓርግ ከፍ ወዳለው እና ለታላቅ ሥልጣን እና የሥራ ሐላፊነት ማድረስ አንዱ መሆኑን ሲምስ እና ስቴፈን (2005፡100) ያሳያሉ።

ራፖርት (1992፡252) ሥርዐት ኹለት ገጽታዎችን ወይም መልእክቶችን ለማስተላለፍ እንደሚረዳ ይገልጻል። የመጀመሪያው በማኅበረሰቡ ዘንድ የማይለወጡ፣ የማይቀየሩ (invariant) የተለያዩ ቀኖናዎችን፣ ሕጎችን፣ ደንቦችን መመሪያዎችን የአቋም ደረጃዎችን ማስገንዘብ ሲሆን ሁለተኛው ከዚህ በተቃራኒ በማኅበረሰቡ ዘንድ ሊሻሻሉ የሚችሉ/የሚለወጡ (variant) የተለያዩ ሕጎችን፣ መመሪያዎችንና ደንቦችን ማመልከት ነው። በዚህ ሥርዐት ውስጥ የፎክሎር የተለዋዋጭነት ባሕሪው ጎልቶ የሚታይበት ነው።

ሥርዐት በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ሊታዩና ሊዳሰሱ የማይችሉ እምነቶችን፣ አመለካከቶችን፣ አስተሳሰቦችን እና እሴቶችን ተጨባጭ በሆነ መልኩ ለማሳየት የሚያስችል ነው። በመሆኑም ሥርዐቱን ለሚያጠና ሰውም ሆነ ለተመልካች

---

[14] Rapport, Ray A. Folklore, Cultural Performances and Popular Entertaiments. (New York: Oxford University Press, 1992).

[15] ጉዳዩን በተመለከተ ሲምስ እና ስቴፈን (2005:95) Rituals are performances that are repeated, patterned and frequently include ceremonial actions that incorporate symbols, actions and repetition በማለት አብራርተው ገልጸዋል።

ስለሚፈጸመው ሥርዐት ምንነት ግንዛቤ በማስጨበጥ የአንድን ማኅበረሰብ አጠቃላይ ገጽታ ለማሳየት የሚያስችል መሆኑን ሲምስና ስቴፈን (2005፡96) ገልጸዋል፡፡ ከዚኽ አንጻር የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዐት መኖር አስፈላጊነት

- ካህናት መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ለማድረግ
- የካህናትን የሥልጣን ደረጃ ለመለወጥ
- ካህናት በአገልግሎታቸው ምን ምን ተግባራትን ማከናወን እንደሚገባቸው ለማሳወቅ
- ካህናት እስከ ሕይወት ፍፃሜአቸው ድረስ በጥሩ ሥነ ምግባር ታንፀው ሃይማኖታዊና ባህላዊ ዕሴቶችን መጠበቅ እንዲችሉ ለማድረግ
- የተለያዩ ማኅበረሰቦችንና ግለሰቦችን በማስተማር፣ በመቀደስ፣ በመፈወስ፣ ከበሽታና ከደዌ እስራት እንዲሁም ከርኩስ መንፈስ ነጻ የሚያደርግን ኀይል ለማጐናፀፍ
- የተለያዩ ሰዎችን በነፍስም ኾነ በሥጋ መከራ እንዳይገጥማቸው ጥሩውን መንገድ ለማሳየት፣ ለመምራት፣ የተጣሉትን ለማስታረቅ፣ ክፉዎችን ለመገሠጽ፣ ከክፉ ሐሳብና መንገድ ለመመለስ እንዲሁም የሃይማኖታቸውንና የባህላቸውን ቀኖና ተከትለው ለተተኪው ትውልድ አርአያ ለመኾን ይችሉ ዘንድ የሚያስችላቸውን ጸጋ ለመስጠትና ለመሳሰሉት ጉዳዩች ነው፡፡

## ፪÷፫÷ ክዋኔ (performance)

ክዋኔ ማንኛውም የፎክሎር ገጽታ በቃልና በድርጊት የሚቀርብበት ወይም የሚንፀባረቅበት ቅጥ (mode) ነው፡፡ የክዋኔን ትርጉም ደስታ ተክለ ወልድ "ብጅታ፣ ድርጊት፣ ዝግጅት"[16] በማለት የገለጹ ሲኾን ከዚኽ ትርጉም በመነሣት የቃሉ ጽንሰ ሐሳብ የአንድን ነገር አሠራር፣ አፈጣጠር፣ አቀነባበር የሚያመለክት መኾኑን እንረዳለን፡፡ ክዋኔ ባህልን ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ ሥርዐቶችንና ዕሴቶችን በማኅበረሰቡ ዘንድ ለማስረጽ የሚያስችል ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡ የአንድ ማኅበረሰብ ምሉዕ ትውፊት የሚገለጸው በክዋኔ አማካይነት ነው፡፡ በመኾኑም ባህል ይቀጥል ዘንድ ሥርዐቶች መከወን አለባቸው፡፡

ካፐቻን (1995፡479) የክዋኔን ጽንሰ ሐሳብ ስትገልጽ የአንድን ማኅበረሰብ ጠባይ አጠቃሎ የያዘ፣ የአነጋገር ዘዬ የሚገለጽበት፣ የተለያዩ ማኅበረሰቦች ባህልና

[16]ደስታ ተክለ ወልድ፡፡ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ (ዐዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፷፪) ፣ ገጽ 642፡፡

ሥርዐት የሚስተዋልበት፣ የአንድን ግለሰብም ኾነ ቡድን ማንነት ገልጾ የሚያሳይ ውበት ያለው የሚያስደስትና የሚያዝናና ልማድ ነው ብላለች፡፡ ኬሪን ባርገር (2005፡264) ደግሞ ክዋኔ የተለዋዋጭነት ገጽታ እንዳለው የድርሰትና የክዋኔን ባሕርይ በማስረዳት ይገልጻል፡፡ ይኸውም ክዋኔ አንድን ድርሰት ህልው የሚያደርግ (ሕይወት የሚዘራበት)፣ የድርሰቱን የተለያየ ገጽታ የሚያሳይ፣ የተለዋዋጭነት ባሕርይ የሚታይበት፣ በድርሰቱ ውስጥ ያለውን እውነት ገልጦ የሚያሳይ እንጂ እንደ ድርሰቱ በቋሚነት አንድን ገጽታ ብቻ የሚያሳይ አይደለም፡፡ ይኽም የአንድ ድርሰት ክዋኔ በከዋኙ፣ በዘመኑ፣ በጊዜው፣ በቦታውና በተለያዩ ኹኔታዎች አማካይነት ሊለዋወጥ የሚችል መኾኑን የሚጠቁም ነው፡፡

በክዋኔ ወቅት ማን፣ ምን፣ ለምን፣ ለማን፣ መቼ፣ የት ፈጸመውና እንዴት ተፈጸመ? የሚሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች በምልዓት መመለስ አለባቸው፡፡ እነዚህ በዚኽ ጥናት ውስጥ ትኩረት የተሰጣቸውና የታዩ ሲኾን የጥያቄዎቹ ዐላማ ክህነት ሰጪውን፣ በሥርዐተ ክህነት ወቅት የሚባሉና የሚደረጉ ነገሮችን፣ የክዋኔውን ዐላማ፣ ክህነት ተቀባዮችን፣ ክህነቱ የሚሰጥበትን ቦታና ጊዜ እንዲሁም የአከዋወን ሥርዐተ ሒደቱን የተመለከተ ነው፡፡ የእነዚህ ጥያቄዎች መልሶች የክዋኔን ገጽታዎችና አላባውያን ያመለክታሉ፡፡ የክዋኔ አላባውያን (elements of performance) አንድ ክዋኔ የሚይዛቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች የሚያሳዩ ናቸው፡፡ የአላባውያኑ አቀነጻጀት የሚያመለክተው ቅደም ተከተላዊ ሒደትን ሲኾን የርስ በርስ ተደጋጋፊነታቸው ወይም ተያያዥነታቸው የክዋኔውን ቅርጽ ወይም መዋቅር የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚኽ አላባውያን የፎክሎርን ዐውድ ለማጥናት የሚያስችሉ ነገሮች ሲኾኑ  የሚጠናውን ርእሰ ጉዳይ ምንነት ገልጸው የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ስለኾነም አንድ አጥኚ በፎክሎር ዘውጐች ላይ ጥናት ሲያደርግ እነዚህን አላባውያን መመርመር ይኖርበታል፡፡

አንድ ማኅበረሰብ የሚመራባቸው መርኆዎች በትውፊት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ኅብረተሰቡም የአኗኗር ዘዴው ፎክሎር በያዛቸውና በሚያስተላልፉቸው ዕሴቶች የሚመራ ነው፡፡ እነዚህም የኅብረተሰቡን ባሕርያት የሚገልጹ ተብለው የሚቀመጡ ነጥቦች ሕጎች፣ ደንቦች፣ ባህላዊ ዕሴቶች፣ መመሪያዎች፣ የአኗኗር ሥልትንና የአስተሳሰብ ደረጃን ያጠቃለሉ ናቸው፡፡ እነዚህ የአንድ ማኅበረሰብ  መርኆዎች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት በመደረግ፣ በመከወንና በመገለጽ ነው፡፡ ክዋኔ በሕግ ወይም በደንብ የተገዛ፣ የተገደበ (rule governed) እና የፊት ለፊት ተሳትፎን (face to face interaction) ማለትም የከዋኙንና የተሳታፊውን የፊት ለፊት መገናኘት የሚጠይቅ ነው፡፡ በክዋኔ ወቅት የሚፈጸሙት ድርጊቶች ኹሉ ትእምርታዊ (symbolic) በመኹናቸው ትርጉም (interpretation) ይሰጣቸዋል፡፡

ክዋኔው የተፈጸመበት ዐላማ በክዋኔ ወቅት የነበሩ አጠቃላይ ገጽታዎች የዚያን ማኅበረሰብ ኹኔታ የሚያመለክቱ በመኾናቸው የእነዚህ ጭምቅ ይዘት የክዋኔውን ዐላማ ወይም ተግባር (function) ያመለክታል፡፡

## ፪.፫.፩. የክዋኔ ገጽታዎች

**ሀ. ድርሰት**- ጄፍ ቶድ (1995፡433 ድርሰት ንግግሮች፣ መዝሙሮች፣ በስሜት የሚገለጹ የፎክሎር ዘውጎች፣ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ ግንኙነቶች፣ ማኅበረሰቡ ስሜቱን የሚገልጽባቸውን ቁሳዊም ኾነ መንፈሳዊ ባህሎች የሚያቀርብ ወይም የሚይዝ ጽሑፍ መኾኑን ያስረዳል፡፡ ይህ ሲባል ግን ሁልጊዜ በጽሑፍ ሰፍሮ የሚገኝ ነው ማለት ሳይኾን በአንድ የክዋኔ ሥርዐት ላይ የሚቀርብን ጉዳይ የሚያመለክት የፎክሎር አላባ ነው፡፡

በዚኽ ጽሑፍ ድርሰት የሚያመለክተው በሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔው የቀረበውን (ከፎክሎር ዘርፍ) በሀገረ ሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚካተት ሃይማኖታዊ ሥርዐት ነው፡፡ ሃይማኖታዊ ሥርዐት ሰዎች ሃይማኖታቸውን የሚያፀኑበት፣ ከኃጢአት የሚፈወሱበት፣ የሥጋና የነፍስን ድኅነት የሚያገኙበት… በመኾኑ ይኽንን ሥርዐት እንደ ባህላቸው ቁሳዊና መንፈሳዊ ኹኔታ፣ ምድራዊውንና ሰማያዊውን ዐለም የሚተረጉሙበት መንገድ ያበጃሉ፡፡ ሰዎች የሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔውን ሲያበጁ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ በመንገርና በመግለጽ ነው፡፡ በቃል ያለው እየተረሳ ሥርዐቱ እንዳይጎድል ደግሞ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ፍትሐ ነገሥት፣ መጽሐፈ ዲድስቅልያና ቀሌምንጦስ በተባሉ የሥርዐት መጻሕፍት ጽፈው አስቀምጠዋል፡፡

**ለ. ቴክስቸር (texture)** - ቴክስቸር የከዋኙንና የተሳታፊውን አጠቃላይ ኹኔታና እንቅስቃሴ የሚመለከት ሲኾን ጽሑፋዊ፣ ሥነ ልሣናዊ እንዲሁም አካላዊ ገጽታዎች ይስተዋሉበታል፡፡ በሥርዐተ ክዋኔው ወቅት የሚቀርበው ቋንቋ፣ ዜማ፣ ድምፀትና አጠቃላይ የአቀራረብ ገጽታ፣ የከዋኙ የአቀራረብ ሥልት እንዲሁም የተቀባዮቹ ስሜት እንዴት እንደተንፀባረቀ የሚገለጽበት መኾኑን ዳንደስ (1978፡25-26)፣ ሲምስና ስቴፈን (2005፡136) ገልጸዋል፡፡ ከዋኙና ተሳታፊው አንድን ድርሰት ሲከውኑ በራሳቸው ዘዴ ስለኾነ ክዋኔውን ለማሳመርም ኾነ ለማድመቅ ብለው ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችን ይፈፅማሉ፡፡ ስለዚህ ዋናው የክዋኔ ገጽታ ይቀየራል፡፡ በመሆኑም ቴክስቸር በድርሰቱ ላይ ለውጥ የሚያመጣ ነው፡፡

ሐ. ዐውድ (context) - ሜሪ ሃፎርድ (1995፡328) context "contecxere" ከሚለው የላቲን ቃል የመነጨ መኾኑን በመግለጽ ትርጉሙም "to weave together, interweave, join together, compose" ማለት መኾኑን ገልጻለች፡፡ በመኾኑም ዐውድ የአንድን ተጨባጭ ነገር እንደ ድርና ማግ ርስ በርሱ

ተጠላልፎ ወይም ተወሳስቦ ወይም የርስ በርስ ተያያዥነት ወይም ቁርኝት፣ ለማመልከት የተቀመጠ ገጽታ ነው፡፡

በፎክሎር ዲሲፕሊን ለመጠናት የሚችሉ ኹሉ በዐውድ ላይ የተመሠረተ ጥናት ሊካሔድባቸው እንደሚገባ ጎልድስቲን (1964፡80) ያስረዳል፡፡[17] ዐውድ የሚያነሳቸው ርእሰ ጉዳዮች ሰዋዊ የኾኑና ከሰው ህልውና ጋር የተቆራኙ በመኾናቸው ዘርፈ ብዙ አቅጣጫ አላቸው፡፡ የሰውን ዕውቀት፣ ማንነትና የማኅበረሰብ አደረጃጀት ዐውቆ ትክክለኛውን መረጃ ለማግኘት ደግሞ በቱባው (በዋናው) ማኅበረሰብ

ውስጥ ገብቶ ወይም ተቀላቅሎ ዐውዳዊ ገጽታዎችን መመርመር ያስፈልጋል፡፡

(1993፣215) ፎክሎርን የመተርጐሚያ መንገዶች ማኅበራዊ ዐውድ (social context )[18]እና የኹኔታ ዐውድ (context of situation)[19] መኾናቸውን ማሊኖዊስኪን (1935 [1965]፣ 118) በመጥቀስ ጠቁመዋል፡፡ ማኅበራዊ ዐውድ የሚገለጽባቸው መንገዶች ባህላዊ ኹኔታዎችን የሚያንፀባርቁ በተለያዩ ግለሰቦች መካከል የጋራ የኾኑ የራሳችን የሚሏቸውና የሚያስተሳስሯቸው ነገሮች ናቸው፡፡

ዳን ቤን አሞጽ (1993፡209) ዊልያም ባስኮም (በ1954 ዐ.ም.) ያቀረበውን ጽሑፍ ዋቢ በማድረግ አንድ አጥኚ ተግባራዊ የትንታኔ ሥልትን በመጠቀም የአንድን ነገር አገልግሎት ወይም ተግባር ለመተንተን ቢፈለግ የፎክሎርን ማኅበራዊ ዐውድ በመጠቀም ወይም በማወቅ ትንታኔ መስጠት እንዳለበት አስረድቷል፡፡ አጥኚው በዚህ ውስጥ ሊመለከታቸው የሚገቡ ነገሮችም ጊዜና ቦታ፣ የክዋኔ ቅርጽ፣ የተራኪዎች (የከዋኞች) ማንነት የአድማጮች ወይም የተሳታፊዎች ጠቅላላ ኹኔታ፣ የከዋኙና የተሳታፊዎች ግንኙነት፣ ከዋኙና ድርሰቱ ያላቸው ግንኙነት፣ በክዋኔው ጊዜ የሚታየው ጥበባዊ እንቅስቃሴ ወይም ድራማዊ የአከዋወን ሒደት፣ የአድማጮች ተሳትፎ፣ የተለያዩ የባህል ገጽታዎች የሚኖራቸው ሀገረ ሰባዊ ክፍፍል እንዲሁም የሰዎች ሥርዐትና አስተሳሰብ መኾናቸውን በዝርዝር ጠቁሟል፡፡

---

17 Goldstien, Kenneth S.  A Guide for Field Workers in Folklore. (London: Herbvert Jenkins, 1964).

18 ዳንደስ (፲፱፻፺፫ ) ገጽ ፳፯፡፡

19 ሲምስ እና ስቴፈን (፳፻፯) ገጽ ፻፴፯፡፡

እንደ ቤን አሞጽ ገለጻ ዐውድ የፎክሎርን ትንተና እና ተግባር ወይም አገልግሎት ለማሳየት የሚያስችል የክዋኔ ገጽታ ነው። የፎክሎር ክዋኔ በዐውድ ሲጠና የይዘት ገለጻ፣ ትንታኔ፣ ቅርጽ፣ መዋቅር እና ድርጊት ለማሳየት ያስችላል።በመሆኑም ዐውዳዊ ትንተና ፎክሎርን ይተረጉማል እንጂ አይገልጽም። በፎክሎር ጥናት ድርሰቱን ብቻ መመልከት ርባና የለውም። ከዐውድ ውጪ የኾነ ክዋኔ የለም። በመኾኑም ትክክለኛው አካሄድ ፎክሎርን በማኅበረሰቡ ውስጥ በመመልከት መመርመር የተፈለገውን ጉዳይ ከባህሉ፣ ከማህበረሰቡና ከኹኔታው ዐውድ አንጻር መመልከት ወይም እነዚህን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ማጥናት ነው (ቤን አሞጽ 2005፡210)።

በአንድ ክዋኔ ውስጥ የፎክሎር ዘውጎች ሲገለጹ አንድን ርእሰ ጉዳይ ብቻ የሚያመለክቱ ተደርገው መወሰድ የለባቸውም። ማንኛውም የክዋኔ ድርሰት የሚተላለፈው በጽሑፍ፣ በታሪክ ወይም በባህላዊ ዐውድ ውስጥ ነው። በእነዚህ ውስጥ ሲተላለፉ በየጊዜው እንደ ዘመኑ፣ እንደ ማኅበረሰቡ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ ርእዮተ ዐለምና የአኗኗር ዘይቤ የነበረው እንዳለ ኾኖ ዐዲስ ትርጉም ሊይዙ ወይም ሊጨምሩ ይችላሉ።

ዳን ቤን አሞጽ (2005፡210) ድርሰት ፍቺ የሚሰጠው በዐውድ ላይ የተመሠረተ ፍቺ ሲሰጠው እንደኾነ “The meaning of a text is its meaning on context” በማለት ይገልጻል። ይህም ድርሰት በዐውድ ሲጠና ወይም ሲመረመር ዐውዱ የሚተላለፈውን መልእክት የተለየ (unique) ፍቺ እንዲኖረው ያደርጋል። የተገለጸው ሐሳብ በዐጭሩ “ዐውድ ፎክሎርን የመተርጐሚያ መንገድ ነው” ወደሚል ማጠቃለያ የሚወስድ ነው። ቦውማን (1990፣88) እና ዳን ቤን አሞጽ (1993፣215) ፎክሎርን የመተርጐሚያ መንገዶች ማኅበራዊ ዐውድ (social context)[20] እና የኹኔታ ዐውድ (context of situation)[21] መኾናቸውን ማሊኖዊስኪን (1935 [1965]፣ 118) በመጥቀስ ጠቁመዋል። ማኅበራዊ ዐውድ የሚገለጽባቸው መንገዶች ባህላዊ ኹኔታዎችን የሚያንፀባርቁ በተለያዩ ግለሰቦች መካከል የጋራ የኾኑ የራሳችን የሚሏቸውና የሚያስተሳስሯቸው ነገሮች ናቸው።

ሲምስ እና ስቴፈን (2005፣110-119) እንደጻፉት የተለያዩ ሥርዐተ በዐላት[22]

[20] ማኅበራዊ ዐውዶች የቋንቋ፣ የዕውቀት፣ የዕሴትና የእምነት ሥርዐት፣ የአስተሳሰብ ደረጃ፣ የፍላጐት መጠን፣ የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ በጥቅሉ የአንድ ዐይነት የታሪክ ባለቤትነት የሚገለጽባቸው ናቸው፡ ፡

[21] የኹኔታ ዐውድ የከዋኙን ዕድሜ፣ ጾታ፣ ማኅበራዊ ደረጃ፣ ሥልት፣ አከዋዋን፣ መቼትና ሌሎች ከማኅበራዊ ዐውድ ባነሰ ወይም በጠበበ መልኩ የተለዩ ገጽታዎች መሠረት በማድረግ ትእምርታዊ ፍቺዎችን የምንመለከትበት የዐውድ ዐይነት ነው።

[22] ማንኛውም ሀገረ ሰባዊ ልማድ በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ሲያገኝ እና ሲከወን ritual (ሥርዐተ

ከሚዘጋጅላቸው ገጽታዎች መካከል አንዱ ከነበሩበት ማኅበራዊ ቦታ ወደ ሌላው ወይም ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለመሸጋገር የሚደረጉ ዝግጅቶች (initation rites) ተብለው እንደሚጠሩ ገልጸዋል። እነዚህ የሥርዐት ዐይነቶች ከአንዱ የሕይወት እርከን ወደ ሌላው የሚደረገውን ሽግግር የሚጠቁሙ ክንዋኔዎች ናቸው። ስለ "initation rite" ጌኔፕ (፲፱፻፯) እና ሲምስ (2005) ከአንድ ማኅበረሰባዊ ቦታ ወደ ሌላው ሽግግር ሲደረግ የሚፈጸሙ ዝግጅቶችን ወይም ድርጊቶችን የሚመለከት እንደኾነ ገልጸዋል። ከዚህ በመነሣት በሥልጣነ ክህነት ተዋረድ አንድ ግለሰብ የዲቁናን፣ የቅስናና የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ለመቀበል የሚያልፍባቸው ሥርዐቶች initation rites ናቸው ማለት ይቻላል።

ሥርዐተ በዐላት እንደ ሲምስ እና ስቴፈን አገላለጽ ሥርዐቶች በግልጽና በይፋ የሚፈጸሙ እንዲሁም ደግሞ በምሥጢር የሚፈጸሙ ሥርዐተ ክዋኔዎች ያሉት ሲኾን የአንድ ቡድን አባላት የሚያደርጉትን የሽግግር ደረጃ ተመርኩዞ በሥርዐቱ ላይ የሚፈጸሙ ቅደም ተከተላዊ ቅንጅቶችን የሚመለከት መኾኑን እንዲህ በማለት ያስገነዝባሉ።

> Initiation rituals express a person's entrance into membership in a group. Group with initiation rituals are usually well defined, with clear hierarchies and structures, perhaps even laws or rules of conducts. Some initiation ceremonies and rituals are private and secret. Others are open to the public (2005:119).

## ፫. የሥልጣነ ክህነት ቅድመ ሥርዐተ ክዋኔ (Separation)

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት ዐይነቶች ሦስት ሲኾኑ እነርሱም ዲቁና[23]፣ ቅስና[24] እና ኤጲስ ቆጶስነት[25] በመባል

---

በዐል) ይባላል። ሃይማኖታዊ ሥርዐት የአምልኮ ሥርዐትን የሚመለከት ሲኾን ሥርዐተ አምልኮው ጥንት በነበረው የቤተ ክርስቲያን ሥርዐት፣ የክርስትና እምነትና መመሪያ (ሕግ) እና ስብከት ላይ የተለያዩ ትርጓሜዎችን በማከል እንዲሁም ሀገር በቀል በኾኑ የተለያዩ እምነቶች፣ ግንዛቤዎች ወይም አመለካከቶች ላይ ተመሥርቶ እንደሚከበር ዶርሰን (፲፱፻፸፪፣ ፫) ያስረዳል።

[23] ዲቁና ዲያቆን (Diakonia) ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲኾን ትርጕሙም አገልጋይ፣ ተላላኪ፣ ረዳት ማለት ነው። ዲያቆን አገልግሎቱን ለሚፈጽመው ሰው የተሰጠ መጠሪያ ሲኾን አገልግሎቱ ደግሞ ዲቁና ይባላል።

[24] ቅስና ማለት የቅስና የክህነት ስም። ቄስ ስም ነው። ካህን በቤተ ክርስቲያን አገልጋይ፣ ሥጋውን ደሙን አቀባይ ወይንም ስብከትን ሰባኪ፣ ቀዳሽ፣ ገባሬ ሠናይ ቄስ፣ ዋና ኾኖ የሚያገለግል። ተሰማ ሀብተ ሚካኤል፡ ፡ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት። ፳፻፳ ገጽ ፫፻፸፫።

[25]ኤጲስ ቆጶስነት የካህናት አለቃ፣ የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ፣ መምህር ማለት መኾኑን ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ይገልጻል። ተሰማ ሀብተ ሚካኤል። ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት። ፳፻፳ ገጽ ፳፻፵።

ይታወቃሉ፡፡[26]እነዚህ የክህነት ዐይነቶች ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ አንዳቸው ከአንዳቸው በደረጃ የሚለያይ ሲኾን የሚመሳሰሉበት ባሕርያቸው ደግሞ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠት ማስቻላቸው ነው፡፡

ሦስቱ የሥልጣነ ክህነት ዐይነቶች "ሥልጣን" ናቸው ሊባሉ የቻሉበት ምክንያት ሥልጣኑን ለመቀበል የሚደረግላቸው ጥሪ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆኖ በእግዚአብሔር ጸጋ የማሰር፣ የመፍታት፣ የመገዘት እና/ወይም ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንንና ሥርዐተ አምልኮትን የመፈጸም ብቃት ስላላቸው ነው፡፡ እነዚህ የሥልጣነ ክህነት ዐይነቶች በዘፈቀደ ለኹሉም የሚሰጡ ሳይኾኑ ለተመረጡና ፈቃደኛ ለኾኑ ወንዶች ብቻ የሚሰጡ ሰማያዊ ሹመቶች ናቸው፡፡ በመኾኑም እነዚህ ካህናት ሥልጣነ ክህነቱን ሲቀበሉ መንፈስ ቅዱስ ያድርባቸዋል፡፡

ይህም እንደ ሥልጣን ዐይነቱ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን የመፈጸም፣ ሰዎችን ከኃጢአት የማንጻት፣ ከክፋት መንገድ የመመለስ፣ ከበሽታ የመፈወስ፣ ከተለያዩ እስራቶች (የርኩስ መንፈስ) የመፍታት እና ሌሎች በሰው አእምሮና ችሎታ ሊፈጸሙ የማይችሉ የተለያዩ ነገሮችን የማከናወን ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

በሥልጣነ ክህነት ውስጥ በክህነት የሚገኘውን መዓርግ ወይም ሥልጣን ለመቀበል ምን ምን ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው? እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ለመረዳት የዲቁና፣ የቅስናና የኤጲስ ቆጶስነት ገጽታዎችን መተንተን

ይገባል፡፡ ዲቁና ከሦስቱ የሥልጣነ ክህነት ዐይነቶች ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጥ ነው፡፡ አንድ ሰው የዲቁናን ሥልጣን ለመቀበል ከአስተዳደጉ ጀምሮ

እንዲጠብቃቸውና እንዲፈጽማቸው የሚጠበቁበት ሕጎችና ምግባሮች አሉ፡፡ መወለድ ሥልጣነ ክህነትን ለመቀበል የሚያስችል የተለየ ገጽታ የለውም፡፡ ምክንያቱም ኹሉም ሰው ይወለዳልና፡፡ ሥልጣነ ክህነትን ለመቀበል ምክንያት ወይም መሥፈርት ሊኾኑ የሚችሉ ከመወለድ በኋላ የሚኖሩ የተለያዩ ክንዋኔዎች

[26]ሊቀካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ፡፡ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን፡፡ (ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፣ ፲፱፻፹፬)፡፡

ሲኾኑ እነርሱም ክርስትና መነሣት (ሥርዐተ ጥምቀትን መፈጸም)፣ የአብነት ትምህርት መማርና በድንግልና፣ በንጽሕናና በበጎ ምግባር መኖር ናቸው።

## ፫.፩፥ ሥርዐተ ጥምቀት መፈጸም (ክርስትና መነሣት)

ጥምቀት ለወንዶችም ኾነ ለሴቶች የታዘዘ ሥርዐት መኾኑን ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ሦስት ያስረዳል። በመኾኑም ሥርዐተ ጥምቀት ለክርስቲያን ኹሉ የሚፈጸም ሥርዐት ነው። በዚህም መሠረት ሥልጣነ ዲቁናን መቀበል የሚችሉ ኹሉ ክርስትና መነሣት አለባቸው።

ጥምቀት ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ ላይ የሚፈጸም ሲኾን የክርስትና ሕይወትን ለመጀመር በቀዳሚነት የሚፈጸም ሥርዐት ነው። በዐዲስ አበባ ከተማ በደብረ ብሥራት (ብሥራተ) ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ግንቦት ፳ቀን ፳፻፫ ዐ.ም. የክርስትና አነሣሥ ሥርዐተ ክዋኔ ምልከታ ሙሉ መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ በትንታኔው የተገኘው ፍሬ ነገር ጥምቀት በሥላሴ ስም በተጸለየበት እና ከሥላሴ መወለድ ወደሚያስችል የተለወጠ ውኃ (ማየ ገቦ) መጠመቅ ነው። ወደ ውኃው ውስጥ መግባት ከክርስቶስ ጋር በሞቱ አንድ መኾን ሲኾን ከውኃው መውጣት ደግሞ ከክርስቶስ ጋር የመነሣት ምሳሌ ነው። እንዲሁም በዘመነ ሐዲስ ኢየሱስ ክርስቶስ (ዮሐ ፫፥፭) "ከውኃና ከመንፈስ ዳግመኛ ካልተወለዳችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አትችሉም" በማለት አስተምሯል። በመኾኑም ሥርዐቱ ለክርስቲያኖች ኹሉ ይፈጸማል። ክርስትናውን ለመቀበል የሚፈጸሙ የተለያዩ ክንዋኔዎች በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ አምስት ላይ ተጽፈው ይገኛሉ።

እነዚህ ክንዋኔዎች የሚፈጸሙት በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ሥርዐቱን ለመፈፀም ተብሎ በተዘጋጀ ወይም በተሠራ የክርስትና ቤት ውስጥ ነው።[27]

## ፫.፪. የአብነት ትምህርት መማር

የአብነት ትምህርት በዲቁና፣ በቅስናና በኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ለማገልገል የሚያስችል ትምህርት የሚሰጥበት ነው። አንድ ሰው ሥልጣነ ክህነት ለመቀበል

[27]ከተሰበሰበው ሙሉ መረጃ ለጥናቱ የሚያስፈልገው ፍሬ ነገር ብቻ ተመርጦ እንዲቀርብ የተደረገበት ምክንያት ከጥናቱ ውስንነት እንዲሁም ይኽን ጥናት ለማቅረብ ከተፈቀደው የገጽ ብዛት አንጻር ነው።

ከፊደል ጀምሮ እስከ መዝገብ ቅዳሴ፣ መዝሙረ ዳዊትን፣ መልክአ መልክእን፣ ሰዐታትን በንባብና በዜማ መማር ይጠበቅበታል። ከዚህም በተጨማሪ የቅዱሳት መጻሕፍትንና መጽሐፍ ቅዱስን መማር እንዲሁም የቅዱሳንን ገድላት በተወሰነ ደረጃ እንኳ ማወቅ ይጠበቅበታል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን ከኾኑት ከብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ጋር ግንቦት ፳፫ ቀን ፳፻፫ ዐ.ም. በተደረገው ቃለ መጠይቅ አንድ ግለሰብ የክህነትን ሥልጣን ለመቀበል ሊያውቃቸው የሚገቡ የቃል ትምህርቶች እንዳሉ ገልጸዋል። እነርሱንም አንድ በአንድ ሲያስረዱ ለቃል ትምህርቶች መግቢያ የኾኑት በስመ አብ፣ ነአኩተከ፣ አቡነ ዘበሰማያት፣ ጸሎተ ሃይማኖት... ያሉ ሲኾኑ ሌሎች ደግሞ ከሰኞ እስከ እሑድ ያሉት ውዳሴ ማርያም፣ አንቀጸ ብርሃን፣ መልክዐ ማርያም፣ መልክዐ ኢየሱስ፣ አባ ጊዮርጊስ የደረሱት ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ጀምሮ የሚጸለይ ሰዓታት እንዲሁም የዜማና የቅዳሴ ትምህርቶች መኾናቸውን ተናገረዋል።

ዲያቆናት ማዕርገ ዲቁና ከመቀበላቸው በፊት የሚማሩት ትምህርት ምን እንደሚመስል ለመመልከት ግንቦት ፰ ቀን ፳፻፫ ዐ.ም. ዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ታእካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም የቅዳሴ ትምህርት መማርያ ቦታ በመገኘት ኹኔታውን ተመልክቻለሁ።

የቅዳሴ መምህሩ መምህር የማነ ብርሃን እንደነገሩኝ በዚያ ቦታ የሚማሩት የቅዳሴ ትምህርት ግብረ ዲቁና፣ መዝገብ ቅዳሴና አጠቃላይ የቅዳሴ ትምህርቶች ሲኾኑ ትምህርቱ የሚሰጠው ከሰኞ እስከ ዐርብ ጧትና ከሰዐት ነው። የተለያዩ ዝግጅቶችና ክብረ በዐላት ሲኖሩ ግን ተማሪዎች ለአገልግሎት ስለሚሔዱ ትምህርት ላይኖር ይችላል።

በመምህር የማነ ብርሃን ጌታ ግራና ቀኝ የተቀመጡ ተማሪዎች የተለያዩ ዜማዎችን የሚያጠኑ ሲኾን ኹለቱ ቡድኖች ካላቸው ልምድ የተነሣ አንዱ የአንዱን ድምፁ በመስማት ትምህርቱ አይደበላለቅባቸውም። መምህሩ ለማስተማር የፈለጉትን የቅዳሴ ዜማ ሲያሰሟቸው በጥንቃቄ እየደጋገሙ በማዜም እስከ መጨረሻው የሚዘልቁት ሲኾን በዜማ የሚናገሩትን ቃል ከመጽሐፈ ቅዳሴ በማንበብ ያጠናሉ። መምህር የማነ ብርሃን የቅዳሴን ዜማ ከማስተማር ጥልቅ ችሎታቸው የተነሣ ኹለቱ ቡድኖች የሚያዜሙትን ዜማ በአንድ ጊዜ በመስማት የተሳሳተውን ለይተው ተማሪዎቹ እንዲያስተካክሉ የማድረግ ብቃታቸው ከፍተኛ መኾኑን ተመልክቻለሁ።

እንደ መምህር የማነ ብርሃን ገለጻ ተማሪዎቹ በመጀመሪያ ግብረ ዲቁና የተባለውን

በግእዝ፣ በዕዝልና በዐራራይ ዜማ የሚዜም የቅዳሴ ትምህርት የሚያጠኑ ሲኾን ይዘቱም በቅዳሴ ጊዜ ዲያቆናትና ሕዝቡ የሚያዜሙትን ዜማ የያዘ ነው፡፡ ኹለተኛው ክፍል መዝገብ ቅዳሴ የሚማሩበት ሲኾን በመጀመሪያው ክፍል ከተማሩት በተጨማሪና በሥርዐተ ቅዳሴ ጊዜ "ይበል ካህን" የሚለውን ክፍል የሚያጠኑበት ነው፡፡ ሦስተኛው ደግሞ በኹለቱ ክፍሎች ውስጥ የተማሯቸውን ትምህርቶች በመምህራቸው አጋዥነት እየከለሱ ትክክለኛውን የቅዳሴ ዜማ የሚማሩበት ነው፡፡ እነዚህን ትምህርቶች ተምሮ ለመጨረስ የተማሪዎች ብቃት የሚወሰነው እንደችሎታቸው ነው፤ ከወራት ጀምሮ እስከ ዐመታት የሚቆጠር ጊዜ ሊፈጅባቸው ይችላል፡፡ በመኾኑም የጊዜ ገደብ ተሰጥቶት በዚህ ቀን ማለቅ አለበት የሚባል አይደለም፡፡

በመንበረ ፓትርያክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከሚያገለግለው ዲያቆን ጽጌ ረዳኢ ጋር ግንቦት ግንቦት ፱ ቀን ፳፻፫ ዐ.ም. ከተደረገው ቃለ መጠይቅ በተገኘው አስረጅ የዲቁናን ሥልጣን ለመቀበል በቅድሚያ ፊደል ከዚያም ደግሞ አቡጊዳና መልእክተ ዮሐንስን በቊጥር፣ በግእዝ፣ ከግእዝ ንባብ ወደ ውርድ ንባብ፣ ከውርድ ንባብ ወደ ቁም ንባብ እያለ እንዳጠናቀቀና ከዚያ በኋላ ወደ ብራና ጽሑፎች በማለፍ የቊጥር፣ የውርድ ንባብ እና ቁም ንባብ እንዳነበበ አስረድቶኛል፡፡ ከዚያም ዳዊትን "ፍካሬ ዘጻድቃን ወዘኃጥአን" እያለ በመጀመር ከጨረሰ በኋላ መምህሩ "አንብበው" የሚል መመሪያ ሲሰጡ መቶ ሃምሳውን የዳዊት መዝሙራት ንባባት እንደዚሁ አጠናቆ እንዳነበበ ገልጾልኛል፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ የሌሊት ትምህርት ሲኾን በዚያም ውዳሴዎችን ከ"በስመ አብ" ጀምሮ እስከ "መልክአ ኢየሱስ" ያሉትን በቃል አጥንቷል፡፡ እንዲሁም "ሰላም ለኪ" ብሎ የሚጀመረውን ውዳሴ ማርያም በዜማ በማጠናቀቅ ከሰኞ እስከ እሑድ ያሉትን በቃል አጥንቷል፡፡ በመጨረሻም መስተጋብዕ፣ አርባዕት፣ አርያም፣ ሠለስት ወዘተ የተባሉ የዜማ ይዘቶችን ጾመ ድጓ ጭምር በመማር የቅዳሴ ትምህርቶችንም የቤተ ክርስቲያን ሥርዐት በሚፈቅደው መሠረት አጠናቆ ማዕርገ ዲቁና እንደተሰጠው አብራርቶልኛል፡፡ክህነትን ለመቀበል የቅዳሴ ዜማ ትምህርት መከታተልና ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ቅዳሴ የሕዝቡ ኃጢአት የሚሰረይበት፣ ከበሽታቸው የሚፈወሱበት፣ ጸሎታቸው ወደ አምላካቸው የሚያርግበት፣ በተለይ ሥጋ ወደሙ የሚፈተትበት (ወይኑና ኅብስቱ አማናዊ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም የሚኾንበት) በመኾኑ ይኽንን ሥርዐት ለማስፈጸም ይችሉ ዘንድ ነው፡፡[28] የቅዳሴውን ዜማ ሲማሩ የያሬድን የዜማ ሥልት ይዞ ትክክለኛውን ቅዳሴ መቀደስ ይረዳ ዘንድ የሚያስችል ትምህርት ይሰጣል፡፡

---

[28](ማቴ ፳፰÷፲፱-፳) የሕዝቡን ኃጢአት የማስተስረይ፣ የቅድስናን ጎዳና የማሳየት፣ (ዮሐ ፳÷፳፫)፣ (፩ኛ ጴጥ ፩÷፲፯) እና ምእመናንን የመጠበቅ (ዮሐ ፳፩÷፲፭-፲፯) ሥልጣን የተሰጣቸው በመ§ኑ አስቀድመው እነርሱ ራሳቸው የዕውቀቱ ባለቤት መኾን አለባቸው፡፡

## ፫.፫. ንጽሕናና መልካም ሥነ ምግባር

በቤተ ክርስቲያን ሥርዐት አንድ ግለሰብ ከማግባቱ በፊት ከሴት ጋር መገናኘት አይፈቀድለትም። ዲያቆን ለመኾን በንጽሕናና በቅድስና መኖር ያስፈልጋል።[29] ከጋብቻበፊትከሴትየደረሰወንድለሥልጣነዲቁናሊበቃአይችልም።ፍትሐነገሥት[30] ላይ ዲያቆን አንዲት ሴት ያገባ ቤተሰቦቹንና ልጆቹን በሚገባ የሚያስተዳድር ይኹን ሲል ይገልጻል። ለዚህ ጥናት ከሰበሰብኳቸው መረጃዎች እንደተገነዘብኩት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት አንድ ምእመን ትዳር ሳይመሠርት በድንግልና የዲቁና ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል። ምክንያቱም ከክህነት ደረጃዎች የመጀመሪያው በመኾኑና ዲያቆኑ ወደፊት የጵጵስናን ሥልጣን ለመቀበል ቢፈልግ ድንግል መኾን ስለሚጠበቅበት ነው። ይህ የሚኾንበትም ምክንያት አሁን ባለው የቤተ ክርስቲያን ሥርዐት ኤጲስ ቆጶሳት ደናግላን መኾን ስላለባቸው ነው። ይኽም የኾነው ሐዋርያት በዘመነ ሐዲስ በንጽሕና ኾነው አገልግሎት ይሰጡ እንደነበር በማሰብ የእነርሱ ደቀ መዛሙርት ለመኾንና አርአያነታቸውን ለመከተል ነው። አንድ ዲያቆን ወደ ቀጣዩ የሥልጣን እርከን ለመሻገር ቢፈልግ መሥፈርቶችን ካሟላ በኋላ የቅስናን ሥልጣን ለመቀበል ይችላል።

የቅስናን ሥልጣን ለማግኘት አንድ ወንድ ያለነውር በአንዲት ሴት ተወስኖ መኖር እንደሚገባው፣ ሕይወቱ በጥሩ ሥነ ምግባር የታነጸ፣ በትምህርቱም አራቱን ወንጌላት በሚገባ ያወቀ እንዲሁም ዕድሜው ደግሞ ሠላሳ ዐመት የሞላው መኾን እንዳለበት ፍትሐ ነገሥት[31] ይገልጻል። አሁን ባለው ተጨባጭ ኹኔታ ደግሞ አንድ ዲያቆን ካህን (ቄስ)

ለመኾን ከኹለት በአንዱ አቅጣጫ መኖር ይጠበቅበታል። ግለሰቡ ዲያቆን

ከኾነ በኋላ በሥልጣኑ ምልዓት ያለው አገልግሎት በመስጠት በንጽሕና መኖር ቀጥሎም ሚስት ካገባ በኋላ ለቅስና የሚያበቁ ትምህርቶችን በመማር ዕውቀት ማግኘት ወይም በድንግልና ሳለ ገዳም በመግባት መመንኮስና የክህነት ትምህርት በመማር ቄስ መኾን ነው። የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ታእካ ነገሥት በኣታ

[29](ጢሞ ፫÷፰-፲፫) ዲያቆናት ትዕግስት ያላቸው፣ ቁጡ ያልኾኑ፣ ነውር የሌለባቸው፣ የማይሰክሩ፣ ሐሰት የማይናገሩ፣ የሚታዘዙ፣ ትጉህና ቅን መኾን እንደሚገባቸው ያስረዳል።

[30]ዐንቀጽ ፪፻፴፱ ገጽ ፸፯

[31] ዐንቀጽ ፪፻፩ ገጽ ፸፩

ለማርያም ገዳም የስብከተ ወንጌል ሓላፊ ቀሲስ ዐለም እሸት ... አንድ ዲያቆን ቄስ ኾኖ ለማገልገል ሚስት ማግባት እንዳለበት ሲገልጹ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> አንድ ካህን ሚስት የሚያገባው በዲቁና እያገለገለ ሳለ ኾኖ ልክ ሚስት አግብቶ ከሠላሳ ዐመት በኋላ የቅስና ሥልጣን መቀበል ይችላል፡፡ የቅስናን ሥልጣን ለመቀበል ይኽ ዲያቆን ጋብቻውን በሥርዐተ ተክሊልና በቅዱስ ቁርባን መፈጸም አለበት እንጂ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዐት ውጭ በኾነ ጋብቻ ቄስ መኾን አይችልም፡፡ ማግባት ያለበትም አንዴ ነው፡፡[32] ቀሲስ ዐለምእሸት ከዚህ መሥፈርት በተጨማሪም ቅስና ለመቀበል ዐራቱን ወንጌላት ጠንቅቆ በማወቅ የተለያዩ ጸሎቶችን፣ ቅዳሴዎችን ማለትም ኪዳን፣ መስተብቍዕና ሊጦን የተባሉትን በቃል መያዝ ወይም ተምሮ መገኘት ይገባል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የትርጓሜ መጻሕፍት መምህር ከኾኑት ከሊቀ ማእምራን ደጉ ዐለም ካሣ ጋር ግንቦት ፲፮ ቀን ፳፻፫ ዐ.ም. በተደረገው ቃለ መጠይቅ ደግሞ አንድ ካህን የቅስና ሥልጣን ለመቀበል በቅድሚያ ለዚህ ሥልጣን የሚመረጥበት ሥነ ምግባር ሊኖረው እንደሚገባ፣ ለሕዝብ የተለያዩ ትርጓሜዎችን የሚያሳውቅበት የዕውቀት ደረጃው ከፍ ያለ፣ ብሉይና ሐዲስን ጠንቅቆ በማወቅ በተለያዩ ቋንቋዎች ተጠቅሞ ሊያስተምር የሚችል መኾን እንዳለበት ገልጸዋል፡፡ በሥነ ምግባርና በጠባይም በኩል የመጠጥ ሱስ፣ ቁጣ፣ ጥልና ጸብ የመሳሰሉትን ማስወገድ ዋና ዋና መመዘኛ ነጥቦች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡
የክህነት ከፍተኛ ደረጃ የኾነውን የኤጶስ ቆጶስነት ሥልጣን ለመቀበል ወይም ለማግኘት የሚያስችሉ ኹለት አማራጮች አሉ፡፡ እነሱም፡-

፩ኛ. ንጽሕናን ጠብቆ በቅድስና ማገልገል እንዲሁም ሚስት ሳያገባ ወይም ከሴት ሳይደርስ ገዳም ሒዶ በመመንኮስ ካህን (ቄስ) መኾን

፪ኛ. የዲቁናን ሥልጣን ሳይቀበል ገዳም መግባትና መማር፣ ንጽሕናውን ጠብቆ፣ ሥርዐተ ምንኲስና መፈጸም፣ ከዚያ በኋላ ዲያቆንና ቄስ መኾን ናቸው፡፡ በኹለቱም አማራጮች ውስጥ ድንግልና፣ ምንኲስናና ክህነት አይቀሬዎች ናቸው፡፡ ክህነቱ ለአገልግሎት፣ ምንኲስናው ዐለምን ንቆ ለመተው ሲኾን ድንግልናው ደግሞ ለንጽሕና፣ ክርስቶስንና ሐዋርያትን ለመምሰል ነው፡፡

---

[32] ግንቦት ፲፮ቀን ፳፻፫ ዐ.ም. ዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ታእካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም የተደረገ ቃለ መጠይቅ፡፡

በፍትሐ ነገሥት እንደተደነገገው በምንኲስና ሥርዐት ውስጥ ከሚፈጸሙ ዐበይት ሥርዐቶች መካከል ግንዘት[33] እና ፍትሐት[34] ኹለቱ ናቸው። ይኽ የሚከናወነው ዐለምን ትተው ወደተለየ ሕይወት መግባታቸውንና እንደሞቱ ተደርገው መቈጠራቸውን ለማመልከት ነው። የቀደመውን ዐለም ትተው ዐዲስ ሕይወት መጀመራቸውን ለማመልከትም ፀጕራቸውን ተላጭተው ቆብ ያደርጋሉ፤ ወይባ (ቢጫ) ልብስ (ቀሚስ) ይለብሳሉ። ለጽጽስና መዓርግ እስኪበቁ ድረስ ቀሪ ሕይወታቸውን የሚያሳልፉት በገዳም ውስጥ በጾምና በጸሎት ነው። መነኰሳት ይኽንን መዓርግ ማግኘት ይችሉ ዘንድ በገዳም የሚኖሩ፣ ለዚህ ዐለም ብዕል የማይጓጉ ወይም ዐለምን ንቀው የተው፣ ሰማያዊውን ሕይወት ብቻ እያሰቡ የሚኖሩ መኾን አለባቸው። መነኰሳት ኤጲስ ቆጶስ ለመኾን በገዳም ውስጥ ከዝቅተኛ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የአስተዳደር ደረጃ (አበምኔትነት) ማገልገል ይጠበቅባቸዋል።[35] ይኽም ወደፊት ቤተ ክርስቲያንን በአግባቡ ማስተዳደር እንደሚችሉ ያስመሰክርላቸዋል። ብዙ የሕይወት ልምድ እንዲኖራቸውም ዕድሜያቸው ከሃምሳ ዐመት በታች ባይኾን ይመረጣል።[36] ከዚህ በተጨማሪም ብሉይንና ሐዲስን፣ ቅዳሴያትን ኹሉ ጠንቅቀው የሚያውቁ እንዲሁም በሥነ ምግባርና በመንፈሳዊ ዕውቀት የበሰሉ መኾን ይገባቸዋል።

## ፬. የዲቁና፣ የቅስናና የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐት

የዲቁና፣ የቅስናና የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐት የሚፈጸምበት ቦታ (መቼት) ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። በቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ሥርዐቶች ሲጀመሩ ቀጣዩ ሒደት የተሳካ ይኾን ዘንድ ፈጻሚዎቹና ተሳታፊዎቹ የመንፈስ ንጽሕና፣ ቅድስናና ደኅንነት ማግኘት ይችሉ ዘንድ ቡራኬ መስጠት ዘወትር የሚፈጸም ተግባር ነው። የዲቁና፣ የቅስናና የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን በሚሰጥበትም ወቅት ሥርዐቱ የሚጀመረው በጸሎተ ቡራኬ ነው። በሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሒደት የሥርዐተ ክዋኔው ድርሰት ቃላዊ (verbal)፣ ጽሑፋዊ (written) እና ምልክታዊ (non verbal)፤ ተምሳሌታዊ (symbolic) በሆኑ ቅርጾች

---

[33]ግንዘት የሞተ ሰውን ወደ መቃብር ለማሰናበት ዐጥቦ በልብስ መገነዝ [መሸፈን]። (ተሰማ ሀብተ ሚካኤል፡ ፡ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የማርኛ መዝገበ ቃላት፣፳፻፫)፣ ገጽ ፲፩፻፹፫።

[34] ፍትሓት ማለት ቀሳውስት የሞተ ሰውን መፍታት፣ ጸሎት ማድረግ ነው። [መሸፈን]። ዝኒ ከማሁ፣ ፲፫፻፸፬።

[35]ፍትሐ ነገሥት፣ ዐንቀጽ ፰፣ ገጽ ፵።

[36]መጽሐፈ ዲድስቅልያ ዘአበዊነ ሐዋርያት። (ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣፳፻፬)፣ ገጽ ፳፫።

የቀረቡ ናቸው:: እነርሱም የሚነበቡት በጽሑፍ ያሉ መመሪያዎች፣ በቃል የሚባሉት ጸሎቶችና ንግግሮች እንዲሁም ትእምርታዊ ፋይዳ ያላቸው ድርጊቶች ናቸው::

## ፬. ፩. የሥልጣነ ዲቁና አሰጣጥ ሥርዐት

የዲቁናን መዓርግ ይሰጥ ዘንድ የተፈቀደለት ኤጲስ ቆጶስ ነው:: የዲቁና አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔን ለመመልከት ግንቦት ፳ ቀን ፳፻፫ ዐ.ም. በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም በአካል ተገኝቼ ነበር:: በዕለቱ ማዕርገ ዲቁናውን ይሰጡ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ[37] ነበሩ:: ሥርዐቱም ከሌሊቱ ፲፩ ሰዐት ላይ የተጀመረ ሲኾን በሊቀ ጳጳሱ ጸሎተ ቡራኬ ተጀመሯል:: ከዚያም ዲቁና የሚቀበሉት ወጣቶች ከሊቀ ጳጳሱ ፊት ለፊት በመቆም ተራ በተራ የክርስትና ስማቸውን ተናገሩ::[38]

በመቀጠልም አቡነ ቀውስጦስ ፊታቸውን ወደ መቅደሱ፣ ሥልጣነ ዲቁና የሚቀበሉት ደግሞ ፊታቸውን ወደ እርሳቸው አዙረው ጸሎት መጸለይ ጀመሩ:: ሥርዐተ ጸሎቱ የተፈጸመው በንባብ ሲኾን ውስጣዊ ይዘቱም ዲያቆናቱ እግዚአብሔርንና ሰውን ማገልገል እንዳለባቸውና አጠቃላይ ተግባሮቻቸውን እንዲያውቁ የሚያስገነዝብ ነው::[39] ይኸም ድሆችን፣ ባልቴቶችን፣ ሽማግሌዎችን፣ እናት አባት የሌላቸውን ይረዱ እንዲሁም ለቄሱና ለጳጳሱ በአክብሮት እና በትሕትና በመላላክ አገልግሎት ይፈጽሙ ዘንድ የሚያዝ ነው::[40]

ከጸሎት በኋላ ሊቀ ጳጳሱ ሥርዐተ ዲቁናውን መፈጸም ጀመሩ:: ዲያቆናት ከዲቁና በፊት የአናጉንስጢስነት፣ የመዘምርና የንፍቀ ዲያቆንነት መዓርጋት ሊቀበሉ ይገባል::[41]

ነገር ግን በዚህ ጊዜ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ሦስቱንም መዓርጋት በዕለቱ በአንድ <u>ጊዜ ሰጥተዋል</u>::[42]

[37] በ፳፻፫ ዐ.ም. ይህ መረጃ ሲሰበሰብ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ የዐዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ረዳት ነበሩ።

[38] በ፳፻፫ ዐ.ም. ይህ መረጃ ሲሰበሰብ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ የዐዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ረዳት ነበሩ።

[39] ከተፈጸሙት ሥርዐቶች ውስጥ ረጅም ሰዐት የወሰደው ይኸ የጸሎት ሥርዐት ነው። ክዋኔውም በግእዝና በዐማርኛ ቋንቋዎች ተፈጽሟል።

[40] ዲቁና የተጀመረው በሐዋርያት ዘመን ሲኾን መሠረቱም ሐዋ ፮÷፩-፮ ላይ ያለው ቃል ነው። "ወልድ ለአብ የምክሩ መልአክና ነቢይ እንደኾነ፣ ዲያቆኑም እንደዚሁ ለኤጲስ ቆጶሱ መልእክተኛና ነቢይ ነው" ተብሎ በዲድስቅልያ እንደተነገረው የዲቁና ማዕረግ አገልግሎት ለመስጠት የሚሾሙት ነው።

[41] አንድ ምእመን ወደ ዲቁና ማዕረግ ለመድረስ ዐራት አገልግሎቶችን መፈጸም ይጠበቅበታል። እነርሱም ዐጻዌ ኆኅት፣ መዘምር፣ አናጉንስጢስና ንፍቀ ዲያቆን ናቸው።

[42] እነዚህን ሹመቶች በአንድ ቀን መስጠት የተጀመረው ኢትዮጵያ የክርስትናን ሃይማኖት ተቀብላ ጳጳሳትን ከግብጽ ታስመጣ በነበረበት ጊዜ ነበር። ይኸም የኾነበት ምክንያት ከግብጽ የሚላከው ጳጳስ አንድ ብቻ በመኾኑ ኹሉንም የሥልጣን ደረጃዎች ጊዜውን ጠብቆ ማዳረስ አስቸጋሪ ስለነበር ኹሉም በአንድ ጊዜ

ጳጳሱ እነዚህን ሥርዐቶች ሲፈጸሙ ለእያንዳንዱ ሹመት የሚኾኑ ጸሎቶችን ጸልየዋል። በእጃቸውም እያሳለሙ ቡራኬ ሰጥተዋል። ለሥርዐተ ሲመቱ የሚጸለየውን የጸሎት ምዕራፍ አንብበው ሲጨርሱና ሹመቶቹን ሲሰጡ "ወእሰይመከ …." ብለው ስማቸውን በመጥራት ሲኾን እነርሱም ሹመቱን መቀበላቸውን ወደ ቤተ መቅደሱ እየዞሩ በመስገድ ገልጸዋል።

በሥርዐተ ክዋኔው ዲያቆናቱ ሰባት ጊዜ ወደ ምዕራብና ምሥራቅ ቦታቸውን እየቀያየሩ የተዘዋወሩ ሲኾን የዚህ ድርጊት ተምሳሌትነት ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ለማመልከት ነው።[43]

ከዚያም ጳጳሱ የዲቁና ሥልጣን ለመስጠት የሚያስችላቸውን ጸሎት ከያዙት መጽሐፍ ውስጥ ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን በየዲያቆናቱ ራስ ላይ ተራ በተራ ጫኑ። ይኽንንም ሲፈጽሙ የቀኝ እጃቸውን በዲያቆናቱ ራስ ላይ ጭነው ከመጽሐፉ የተወሰኑ አንቀጾችን ካነበቡ በኋላ ኹለት እጆቻቸውን አደራርበው በመጫን (በአንብሮተ ዕድ) ለተወሰነ ደቂቃ ወደ ላይ እየተመለከቱ በተመስጦ ጸለዩ።

ይኽም ሥርዐት እንደተፈጸመ ጸሎት ካደረጉ በኋላ በግራ እጃቸው አገጫቸውን፣ በቀኝ እጃቸው ደግሞ መስቀላቸውን በመያዝ ግንባራቸውን፣ አገጫቸውን፣ የግራ ጉንጫቸውንና የቀኝ ጉንጫቸውን ጫን እያደረጉ በማስነካት በትእምርተ መስቀል ባረኳቸው።[44]

በሉቃስ ወንጌል (፲፩÷፪) ላይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ምን በማለት መጸለይ እንዳለባቸው ባስተማራቸው መሠረት በቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ አምልኮት በሚፈጸምበት ጊዜ "አባታችን ሆይ" ተብሎ እንዲጸለይ ይደረጋል። በሥልጣን አሠጣጥ ሥርዐቱም ይህ ጸሎት እንዲጸለይ ከተደረገ በኋላ ፲፪ ጊዜ "እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ" እንዲሉ አዘዟቸው።[45]

ሲሰጥ ቆይቷል። ይኽ ልማድም እስካሁን ቀጥሎ እየተሠራበት ነው።

[43] በእያንዳንዱ የሹመት አሰጣጥ ፍጻሜ ሥልጣነ ክህነት የሚቀበሉት አካላት ወደ ቤተ መቅደሱ ዞረው መስገዳቸው ለአምኮተ እግዚአብሔር መግለጫ መኾኑን እንዲሁም ወደተለያዩ አቅጣጫዎች መዟዟራቸው ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው ወቅት በተለያዩ አቅጣጫዎች ተዘዋውሮ ማስተማሩን ለመግለጽ ሲኾን እነርሱም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይኽንን ተግባር ለመፈጸም ሓላፊነት የተጣለባቸው መኾኑን ለማጠየቅ እንደኾነ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መምህር ደጉዐለም ካሣ ግንቦት ፳፮ ቀን ፳፻፲ዐ.ም. በተደረገው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል።

[44] በዚህ ጊዜም በግእዝ የሚጸልዩት ጸሎት ነበር። ይኽ ሥርዐትም ጸጋ እግዚአብሔርን የሚያገኙበት፣ ሥልጣነ ዲቁናውን በጳጳሱ አማካይነት የሚቀበሉበትና መንፈስ ቅዱስ ወርዶ በእነርሱ ላይ እንዲያድር የሚደረግበት መኾኑን ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ ገልጸውልኛል።

[45] ፲፪ ጊዜ "እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ" የሚለውን ጸሎት በቤተ ክርስቲያን የተገኙ ኹሉ ያደርሱታል። በቤተ ክርስቲያን ሥርዐት እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ሲባል በተለምዶ ዐራቱን ጣቶች በመዘርጋት በአውራ ጣት የጣቶችን አጽቅ በመንካት ነው። የጣት አጽቆቻቸውን ከላይ ወደታች እየነኩ መውረዳቸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማያት ወደ ምድር መምጣቱን፣ ከዚያም ከታችኛው አጽቅ ተነስተው

ይኽ እንደተጠናቀቀም ሊቀ ጳጳሱ ዲቁና ተቀባዮቹን ወደ እርሳቸው ጠጋ እንዲሉ በማድረግ "በድፍረት ቤተ ክርስቲያን ገብቼ አገለግላለሁ፣ ንጽሕናዬን አጎድፋለሁ፣ በሥውር ኃጢአት እሠራለሁ ብትሉ በስውር የሚያይ እግዚአብሔር ኃጢአታችሁን ይይዝባችኋል። ክህነት የማይደገም ምሥጢር ነውና ክህነታችሁን የሚያጎድፍ ተግባር አትፈጽሙ። እግዚአብሔርንና ሰውን በቅንነት አገልግሉ። ይኽንን ባታደርጉ ግን ምእመናን ጭምር ይከሷችኋል። 'ብርሌ ከነቃ አይኾንም ዕቃ ነውና ይህ አገልጋይ ሊኾን አይችልም' በማለት ይመሰክሩባችኋል። በአንጻሩ ደግሞ መልካም አገልጋይ ከኾናችሁ 'ለከፍተኛ መዓርግ የሚያበቃ ነው፤ እግዚአብሔርንም ማገልገል ይችላል ብለው ይመሰክሩላችኋል" በማለት ቃለ ምዕዳን ሰጧቸው።[46]

አቡነ ቀውስጦስ የዲቁናውን ሥልጣን ሰጥተው እንዳጠናቀቁ ኹሉንም ባረኳቸው። ከዚያም ቀጣዩ ክዋኔ ዲያቆናቱ ሥልጣኑን ከተቀበሉበት ቦታ ወደ ቅድስቱ በማለፍ በወንዶች መቆሚያ[47] በኩል ኹነው ሥርዐተ ቅዳሴውን የተካፈሉበት ሥርዐት ነው። በሥርዐተ ቅዳሴው መካከል ቀዳሹ ካህን ከመቅደስ በመውጣት በመስቀላቸው ባረኳቸው። የዕለቱን ወንጌል ዲያቆናቱና ምእመናኑ እንዲሳለሙ ተደረገ። ወንጌሉን የመሳለማቸው ዐላማ የተነበበውን የእግዚአብሔር ቃል አምነው መቀበላቸውን የሚያመለክት ነው።[48]

ቅዱስ ቊርባን ለማቀበል ወይም ድርገት ሲወርዱ ዲያቆናቱን ከሌሎች ቆራቢዎች ቀድመው ፊት ለፊት ተሰልፈው እንዲቆሙ በማድረግ ለቊርባን አዘጋጇቸው። ቅዱስ ቊርባን ሊቀበሉ ሲሉ ከነጠላቸው በላይ የክህነት ካባ አምጥተው አለበሷቸው።[49] ከዚያም ሥጋ ወደሙን ከምእመናን ቀድመው ተቀበሉ።[50] ሥጋ ወደሙን ተቀብለው ወደየቦታቸው ሲመለሱ ቅዳሴ ጸበል እየተቀዳ ተሰጣቸው። ሥርዐተ ቅዳሴው እንደተጠናቀቀ ዲያቆናቱ ከቤተ መቅደስ በመውጣት በመጠለያው ሥር

ወደ ላይ መውጣታቸው ወደ ሰማይ ማረጉን ያመለክታል። ዐራቱ ጣቶች ሦስት ሦስት አጽቆችን የያዙ ስለኾነ እነዚያ ሲቆጠሩ (፬x፫ = ፲፪) ይኾናሉ። ፲፪ ጊዜ እንዲባል የታዘዘበት ምክንያትም በቀን ውስጥ ፲፪ ሰዐታት ስላሉ ቀኑን ሙሉ ስንሠራው የዋልነውን ኃጢአት ይቅር በለን የሚል ትርጓሜ አለው።

[46] በሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ቃለ ምዕዳን ሥርዐተ ክዋኔው ከተፈጸመ በኋላ የሚተላለፈውን "መልእክት" የሚያሳይ ሲኾን በአጠቃላይ ዲያቆናቱ ለአገልግሎት የሚበቁበትን ኀይል ተጎናጽፈው ምን ምን ተግባራትን ማከናወን እንደሚጠበቅባቸው የሚነገርበት ምሥጢር ነው።

[47] በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የወንዶችና የሴቶች መቆምያ ቦታ የተለያየ መኾኑ ወንዶች ሴቶችን ሴቶች ደግሞ ወንዶችን በመመልከት ሐሳባቸው ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዳይወሰድ፣ በሙሉ ልባቸውና በንጽሕና እግዚአብሔርን ማምለክ እንዲችሉ ነው።

[48] ይኽ ሥርዐት ለምእመናን ኹሉ የሚደረግ ነው።

[49] ይኽም የሚያመለክተው ሥልጣነ ክህነት መቀበላቸውንና ለዚያም ክብር መብቃታቸውን ነው።

[50] ይኽም የኾነበት ምክንያት ማዕረጋቸው ከቀሶች በታች ከምእመን በላይ በመኾኑ ነው።

ተቀምጠው ጸዲቅ (ቁራሽ ዳቦ) ቀመሱ፡፡[51]

ተሳታፊዎች ይኽንን ሥርዐት ሲቀበሉ ቀልባቸውን በመሰብሰብ እያንዳንዷን የጳጳሱን ድርጊት በተመስጦ በመከታተልና በመፈፀም ነው፡፡ ሥልጣነ ክህነት የተሰጣቸው ዲያቆናት በክዋኔው ንቁ ተሳታፊዎች ሲኾኑ በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ግን ሥርዐቱን ከመመልከት በቀር ተሳትፎ ያላደረጉ በመኾናቸው "ፍዝ"[52] ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡

ዲያቆናቱ ሥርዐተ ሲመቱ ሲፈጸምላቸው ምን ተሰምቷቸው እንደነበር ተጠይቀው ሲመልሱ ይኽ ነው የማይባል ደስታና ክብር ተሰምቷቸው እንደነበር ገልጸዋል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ማንም ሰው እንደፈለገው ማግኘት የማይቻለውን ነገር ግን በእግዚአብሔር ሐሳብና ፍቃድ ብቻ የሚሰጥ ሥልጣን ማግኘታቸው እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉበት፣ ለተለየ አገልግሎትም የተጠሩበትና የሚሰማሩበት በመኾኑ ነው፡፡

## ፬.፪. የሥልጣነ ቅስና አሰጣጥ ሥርዐት

የቅስናንም መዓርግ መስጠት የሚችለው ኤጲስ ቆጶስ ነው፡፡ ኤጲስ ቆጶሱ ቅስና ሊቀበል የቀረበው ዲያቆን ከላይ በቀረበው ክፍል ላይ ያሉትን መሥፈርቶች ማሟላቱን፣ ሃይማኖታዊና ሥነ ምግባራዊ ዕሴቶችን መጠበቁን ጊዜ ወስደው መርምረው ካጠናቀቁ በኋላ የቅስናውን ሥልጣን መስጠት ይችላሉ፡፡
ዲያቆኑ ቅስና ለመቀበል ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጣ እንደ ዲቁናው ጊዜ ኹሉ ቅድመ ዝግጅቶችን ማድረግ አለበት፡፡ በሥርዐተ ክዋኔው ወቅት የሚጸለየው ለቅስና የሚያበቃ ጸሎት በሥርዐት መጽሐፉ ውስጥ ይገኛል፡፡ ጸሎቱ ክርስቶስ ለሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን እንዴት እንደሰጣቸውና ቀሳውስት ስለሚያበረክቷቸው አገልግሎች የሚገልጽ ነው፡፡

ሊቀ ጳጳሱና ዲያቆናቱ ክህነቱ በሚሰጥበት ቦታ በምሥራቅና በምዕራብ አቅጣጫ

[51]አንድ ሰው ቆርቦ ከሰዎች ጋር ከመነጋገሩ በፊት ከቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ሳይወጣ እህል በአፉ መቅመስ ያለበት ሥጋ ወደሙን በተቀበለበት አፉ ወሬ ማውራት የተቀበለውን ቅዱስ ቍርባን ማቅለልና ክብር አለመስጠት ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብቶ የተቀደሰበት እህል(ጸበል ጸዲቅ) መቅመስ በረከት ነው ተብሎ ይታመናልና በረከቱንም ለመካፈል ነው፡

[52] በቤተ ክርስቲያን በማናቸውም አገልግሎቶች ውስጥ የሚሳተፉ ሦስት አካላት አሉ፤ ቀሳውሰት፣ ዲያቆናትና ምእመናን፡፡ እያንዳንዳቸው በእነዚህ ሥርዐቶች ውስጥ የተመደቡላቸው "ይ.ካ."፣ "ይ.ዲ. " እና "ይ.ሕ." በሚሉ ምኅጻረ ቃላት የተገለጹ የተሳትፎ ድርሻዎች አሏቸው፡፡ በዚህ የክህነት አሰጣጥ ሥርዐትም ምእመናንን በቀጥታ የሚመለከት ባይኾንም ቢያንስ "አቡነ ዘበሰማያት"፣ "እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ" እንዲሁም ቡራኬ በሚሰጥበት ወቅት ደግሞ "አሜን" በማለት የሚሳተፉ መኾኑ መዘንጋት የለበትም፡
፡

በመዘዋወር ጸሎት ያደርሳሉ። ይኽም በዲቁናው ሥርዐት ላይ እንደተገለጸው ክርስቶስ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ከሰሜን ወደ ደቡብ እየተዘዋወረ ማስተማሩን ለማመልከትና እነርሱም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የእርሱን አርአያ ፍኖት ተከትለው መንዝ እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኹነው አቅጣጫቸውን እየለዋወጡ የሚዟዟሩበትን ቦታ ወይም ቤተ መቅደስ እንደ ዐለም በመቁጠር ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው ወቅት በተለያዩ አቅጣጫዎች ተዟዙሮ ማስተማሩን ለመግለጽ ሲኾን እነርሱም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይኽንን ተግባር ለመፈጸም መንፈሳዊ ሓላፊነት የተጣለባቸው መኾኑን ለማመልከት ነው።

በሥርዐተ ክዋኔው ላይ በፍትሐ ነገሥት ዐንቀጽ ስድስት ላይ በተጠቀሰው መሠረት የቅስና ሥልጣን ሊቀበል የመጣውን ዲያቆን እንዲንበረከክ በማድረግ በአንብሮተ እድ ይባርኩታል። ሌሎች ቀሳውስትም ቀርበው ይዳስሱታል። ይኽም ሥልጣኑን የመስጠት፣ የማስተላለፍና የመባረክ መገለጫ ነው። መንፈስ ቅዱስ በላያቸው ላይ እንዲያድር ለማድረግ የሚፈጸመው ሥርዐት “ንፍኀት” ይባላል። ሊቀ ጳጳሱ “ንሣዕ መንፈሰ ቅዱሰ” በማለት በተቀባዩ ፊት ላይ “እፍ” የሚሉበት ሥርዐት ነው።[53] ከዚህ በኋላ “ቤተ ክርስቲያንን እንድታገለግል ሥልጣን ተሰጥቶሃል” በማለትም ቅስና መቀበሉን ያረጋግጡለታል። ቀጥሎም “እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ” ፲፪ ጊዜ እንዲል እና “አቡነ ዘበሰማያት” እንዲደግም ይደረጋል። ከዚህ በኋላ ሊቀ ጳጳሱ ቃለ ምዕዳን ይሰጣሉ። ይኽም ክህነቱን እንዳይሽር፣ ሃይማኖቱን እንዲጠብቅና ሥልጣኑ በሚያዘው ሕግና ሥርዐት መሠረት መንዝ የሚጠበቅበት መኾኑን እንዲሁም ሰውንና እግዚአብሔርን ማገልገል እንዳለበት የሚያሳስብ ነው። ከዚህ ሥርዐት ፍጻሜ በኋላ የቅስናውን ሥልጣን የተቀበለው ካህን ወደ ቤተ መቅደስ ውስጥ በመግባት ሥርዐተ ቅዳሴውን ተካፍሎ ሥጋ ወደሙን እንዲቀበል ይደረጋል።

ዲያቆን የነበረው ግለሰብ ከዚህ ሥርዐት በኋላ የቅስና ሥልጣን ተቀብሏልና የዚህ ሥልጣን (መዓርግ) መገለጫ የሚኾነውን ነጭ ጥምጥም[54] በራሱ ላይ ይጠመጥማል። በአሁኑ ወቅት ግን መሪ ጌቶች (በቤተ ክርስቲያኗ

[53]ፍትሐ ነገሥት ዐንቀጽ ፯። ይኽን ሥርዐት የሚፈጽሙትም ክርስቶስ ለሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን ሲሰጣቸው መንፈስ ቅዱስን “እፍ” ብሎ እንዲቀበሉ በማድረጉ ነው።

[54] ነጩ ጥምጥም የሚዘጋጅበት ጥሬ እቃ ጥጥ ሲኾን ተዘጋጅቶ ሲታይ የነጠላና ጋቢ ዐይነት አሠራር ያለው ነው እንጂ ለዚህ ዐላማ ተብሎ በሌላ ቀለምና ቅርጽ የሚሠራ አይደለም። ጥምጣሙ በተግባር ላይ ሳይውል እንዲሁ ተዘርግቶ ሲታይ ስስ ነው። በተለምዶ “ሻሽ” ይባላል። ይኽ ሻሽ ቀለሙ በጣም ነጭና ንጹሕ መኾን አለበት። ሻሹን ለማስጌጫ ተብሎ ነጭም ኾነ ሌላ ዐይነት ቀለም ያለው ጥለት ሊደረግበት አይገባም። በዚህ ሻሽ ጥምጣም ሠርተው በራሳቸው ላይ የማድረጋቸው ትርጉም የረድኤተ እግዚአብሔር መገለጫ ተምሳሌትነትን የያዘ ነው። እንዲሁም አንድ ካህን ከሌላው ማኅበረሰብ ተለይቶ የሚሰጠውን ክብር፣ የሥራ ድርሻውን ወይም አገልግሎቱን፣ ምእመን ወይም ካህን መኾኑን ለይቶ እንዲያውቅና አስፈላጊውን መንፈሳዊ እርዳታ ለመጠየቅ እንዲችል የሚጠቅም ነው።

መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች በአንዱ ያስመሰከሩት ካልኾኑ በስተቀር) ጠምጥመው አይታዩም።

## ፬.፫. የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን አሰጣጥ

የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ከዲቁናና ከቅስና መዓርጋት ይበልጣል። በመኾኑም ሥልጣነ ክህነቱን ለመስጠት ከኹለቱ ሥልጣናኖች ከፍ ያለ ዐውድ ይጠይቃል። ሥልጣነ ክህነቱ የሚሰጠው በኹለት ወይም ከዚያ በላይ በኾኑ ሊቃነ ጳጳሳት ወይም ፓትርያርኩ በተገኙበት ነው። የኤጲስ ቆጶስነት መዓርግ የሚሰጠው በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስና በሀገረ ስብከቱ ምእመናን ተወካዮች ለሚመረጡ መነኮሳት (ቆሞሳት) ነው። በምርጫው የሚሳተፉት ምእመናን ዐመት የሞላቸውና ማመዛዘን የሚችሉ ምእመናን መኾን አለባቸው። ምክንያቱም ሊያገለግሏቸውና ሊመሯቸው የሚችሉትን ጳጳሳት በአስተዳደር ብቃታቸው፣ በጥሩ ሥነ ምግባራቸው፣ በዕውቀታቸውና በሕግ (ደንብ) ወይም ሥርዐት አክባሪነታቸውና ጠባቂነታቸው መዝነው የሚበጃቸውን በመምረጥ ማቅረብ እንዲችሉ ነው[55] በሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔው ላይ ተገኝተው ሥልጣኑ የሚገባው ወይም የማይገባው መኾኑን መመስከር እንዲችሉ ሥልጣነ ክህነቱ የሚሰጥበት ቀን ሰዎች በሚሰበሰቡበት በዕለተ እሑድ በሥርዐተ ቅዳሴ ላይ እንዲሆን በፍትሐ ነገሥት ዐንቀጽ ፩ እና በዲድስቅልያ ዐንቀጽ ፳፫ ተወስኗል። ምርጫው የሚፈጸመው በመንፈስ ቅዱስ፣ በጳጳሳትና በምእመናን ነው። ጳጳሳት እንዲመርጡ ሲደረግ ለምሳሌ ዐሥር ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም ተፈልጎ ከኾነ ሃያ መነኮሳት ይቀርባሉ። በኹሉም አህጉረ ስብከት ያሉ ጳጳሳት ተሰብስበው በተሰጣቸው ነጭ ወረቀት ላይ ከሃያዎቹ መነኮሳት የመረጧቸውን ዐሥር መነኮሳት ብቻ እንዲጽፉ ይደረጋል። ለምርጫ ከቀረቡት ቆሞሳት በመንፈስ ቅዱስ መመረጣቸውን የሚያረጋግጠው ዕጣ የወጣላቸው ብቻ የኤጲስ ቆጶስነትን

መዓርግ ያገኛሉ። ይኽ ሥርዐት የሚካሄደው የሚወጡት ዕጣዎች ኹሉ በመንበሩ[56] ላይ ለሰባት ቀናት[57] ተቀምጠው እንዲጸለይባቸውና እንዲቀደስባቸው ተደርጎ ነው።

ምንም እንኳ በሕዝበ ክርስቲያንና በጳጳሳት በኵል በአንደኛ ደረጃ ላይ የተመረጡ ቢኾንም መንፈስ ቅዱስ ካልተጨመረበት ሥልጣኑን መስጠት ፋይዳ እንደሌለው ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ ገልጸዋል። በዚህ መልኩ የተመረጡ

---

[55] መጽሐፈ ዲድስቅልያ ዘአበዊነ ሐዋርያት። (ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ ፳፻፬)፣ ዐንቀጽ ፴፮። ፍትሐ ነገሥት ዐንቀጽ ፬። ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዲን ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ።

[56] ሹመቱ በሚሰጥበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኝ መንበር ላይ ማለት ነው።

[57]ቀናቱ ሰባት መኾናቸው ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለማጠየቅ ነው።

ቆሞሳት ቀን ተወስኖላቸው ሕዝብ በተሰበሰበበት በዕለተ እሑድ በቅዳሴ ሥርዐት ላይ የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ይሰጣቸዋል።

እሑድ ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፺፱ ዐ.ም. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኵሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ሰባተኛ ዐመት የሢመት በዐል በሚከበርበት ዕለት ለዐሥራ ስድስት ቆሞሳት የኤጲስ ቆጶስነት መዓርግ ተሰጥቷል። በማኅበረ ቅዱሳን በድምፅ ወምስል ክፍል በምስል ተቀርጾ የተቀመጠው መረጃ እንደሚያሳየው የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን አሰጣጥ ክዋኔ የሚከተለው ዐይነት ሒደት ነበረው።

ሥልጣነ ክህነቱን ለመስጠት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ከሌሊቱ ዐሥራ አንድ ተኩል ሲል ዐዲስ አበባ በሚገኘው በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ደረሱ። በቦታው ሲደርሱ ሦስት ጊዜ ደወል ተደወለ። የእርሳቸውን መምጣት ሲጠባበቁ የነበሩ ሕዝበ ክርስቲያን፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎች እንግዶች በታላቅ እልልታና ዝማሬ ተቀበሏቸው። አብረዋቸው የመጡ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ፣ አቡነ ጢሞቴዎስ፣ አቡነ ገሪማ፣ አቡነ አትናቴዎስ፣ አቡነ ፊልጶስ፣ አቡነ ጎርጎርዮስ፣ አቡነ መቃርዮስ፣ አቡነ ቀውስጦስና ሌሎችም ጳጳሳት ሲኾኑ ቍጥራቸውም ዐሥራ ሰባት ነበር። ኹሉም ጳጳሳት ልብሰ ተክህኗቸውን ለብሰዋል። በዕለቱ ሥልጣነ ክህነቱን የሚቀበሉት ዐሥራ ስድስት ቆሞሳት ቤተ መቅደስ ውስጥ ገብተው ከመቅደሱ ፊት ለፊት ቆሙ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስም ሕዝቡን እየባረኩ ወደ መቅደስ በመዝለቅ ሦስት ጊዜ ተሳለሙ። ወዲያው ኪዳን አድርሰው የሥርዐተ ጽጽስና አሠጣጥ ሥርዐቱ ተጀመረ። በዕለቱ አቶ ዮሴፍ ወልደ መስቀል ከዐዲስ አበባ መስተዳድር፣ የውጭ ሀገር ዜጎች፣ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላትና በዐዲስ አበባ የሚገኙ የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች እንዲሁም የሌሎች የእምነት መሪዎች ተገኝተዋል። በሥርዐቱ ላይ የተገኙት ሊቃነ ጳጳሳት የለበሱት ቀሚስ ከሐር የተሠራ ወርቃማ (ወደ ቢጫ የሚያደላ) ቀለም ያለው ነው። አንገታቸው ላይ ትልልቅ መስቀል አድርገው አርዌ ብርት ይዘዋል። የጳጳሳቱ አርዌ ብርት[58] ከፓትርያርኩ አርዌ ብርት አጠር ያለ ኾኖ ጫፉ ላይ ድቡልቡል ቅርጽ ያለው ነው።

ሥልጣኑን ከሚቀበሉት ከዐሥራ ስድስት ቆሞሳት አንዱ ሰማያዊ ሌላው ደግሞ

[58] ይኽ አርዌ ብርት ሙሴ ከዐለት ውኃ ያፈለቀበት፣ የኤርትራን ባሕር ለኹለት የከፈለበትና ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት ያሻገረበት ምሳሌ ነው። በመኾኑም ምእመናኑን የመጠበቂያ ምሳሌ ተደርጎ ይታሰባል፡ ፡ ከዚህም በተጨማሪ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስን በዮሐ ፳፩÷፲፭ ግልገሎቼን፣ በጎቼን፣ ጠቦቶቼን ጠብቅ ብሎ በወንጌሉ የተናገረው ቃል ለእርሱ ብቻ ኾኖ የቀረ ሳይኾን የካህናትን ተግባር የሚያመለክት ነው። ግልገሎች በጎችና ጠቦቶችም የምእመናን ምሳሌዎች ሲኾኑ በትሩም ምእመናኑን በሚጠብቁበት ሕግና ሥርዐት የሚመሰል መኾኑን ይገልጻል።

ከዚህ በኋላ ሥርዐቱ ላይ የተገኙት ጳጳሳት ከኋላቸው በመኾን እየዞሩ በቀኝ እጃቸው ትከሻቸውን ጫን ጫን በማድረግ ነኳቸው:: ይኽን ማድረጋቸውም ክህነትን የመስጠት፣ ሜሮን የማፍላትና የመለወጥ፣ ታቦትና ቤተ ክርስቲያንን የመባረክ እንዲሁም የማስተዳደር ሥልጣን፣ ጸጋና በረከት እንዲያድርባቸው ለማድረግ ነው::

ከዚያም በኋላ ካባና አስኬማ ቆብ በጠረጴዛው ላይ በፊት ለፊታቸው ተቀመጠና ተጸለየበት:: ፓትርያርኩ በቅድሚያ ቀሚሱን ከዚያም ሞጣይቱን (በአንገት የሚጠለቅ፣ በኋላ በኩል እስከ ጀርባ፤ በፊት ለፊት በኩል ደግሞ እስከ እግር ጥፍር ድረስ የሚወርድ) ቀጥሎም ካባውን አለበሷቸው:: ይኽ ሥርዐት እንደተጠናቀቀ አስኬማ ቆቡ ተደረገላቸው:: ይኽ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ካህናት ይለብሱት ዘንድ የመረጠላቸውን የአልባሳት ዐይነት[62] መሠረት ያደረገ ነው::

የለበሱት ቀሚስ ከሐር የተሠራ ወርቃማ (ወደ ቢጫ የሚያደላ) ቀለም ያለው ሲኾን የሞጣይቱና የካባው ቀለም ደግሞ ቀይ ኀ፦ንጉርጉር ነው:: አክሊለ ሦኩ (ቆቡ) ደግሞ ከሐር የተሠራ ኾኖ ጥቁር ቀለም አለው::[63]

ይኽ ሥርዐት እንደተፈጸመ ከዐሥራ ስድስቱ ኤጲስ ቆጶሳት መካከል አንዱ ኹሉንም በመወከል የኤጲስ ቆጶስነት አገልግሎታቸውን በሚገባ ለመፈጸም በትጋት እንደሚሠሩ ቃል ገቡ:: የሚፈጽሟቸውን ተግባራት ዝርዝር ከወረቀት ላይ እያነበቡ ቃል ኪዳን የገቡ ሲኾን ከእነርሱም ውስጥ በኒቅያ ጉባኤ በተደነገገው ሥርዐት (ጸሎተ ሃይማኖት) እንደሚያምኑ፣ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አንድ አካል መኾናቸውን፣ ወልድ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ መኾኑን፣ ቅድስት ማርያም የአምላክ እናት መኾኗንና ሌሎችንም መሠረታዊ ትምህርቶች አምነው እንደሚያስተምሩ የሚገልጹ ናቸው:: የቃል ኪዳን ሥርዐቱ ከተፈጸመ በኋላ ቅዱስ ፓትርያርኩ ከዚያን ዕለት ጀምሮ የሚጠሩበትን ስም ለተሿሚዎቹ "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ወእሰይመከ ብፁዕ አባ…" በማለት የሚሰሩበትን ሀገረ ስብከት ጭምር በመግለጽ ሰየሟቸው:: በዚህ ጊዜ ሕዝበ ክርስቲያኑ እያጨበጨቡ "አሜን፣ አሜን" በማለት ፈቃዳቸውን ገልጸዋል::

[62] ሙሴም አሮንንና ልጆቹን በታዘዘው ሥርዐት መሠረት ለክህነት  የተመረጡ ልብሶችን ያለብስ  ነበር:: በዘሌ ፳÷፯-፴፩፣ ዘዳ ፳፳÷፪ በዚያ ዘመን የታዘዙት ሥርዐቶች ሲወርድ ሲዋረድ ለዚህ ዘመን እየተላለፉ የደረሱ ትውፊቶች ናቸው:: በዚያ ጊዜ ለአገልግሎት ሥርዐት እጀ ሰፊና እጀ ጠባብ ቀሚስ፣ ኀ፦ንጉርጉር መደረቢያ፣ መጠምጠሚያ፣ ቆብ፣ ዑሪምና ቱሚም የሚቀመጡበት የደረት ኪስ፣ መታጠቂያ፣ ኤፉድ እና የበፍታ ሱሪ ይለብሱ ዘንድ ያዝዝ ነበር:: አሁን  በከፊል የሚፈጸመው ሥርዐት ያንን ልማድ የተከተለ ነው:: ይኽ ውስጣዊና ውጫዊ ትርጉም ያለው ሲኾን ውስጣዊ ትርጉሙ እንደ የነፍስና የሥጋን ንጽሕና፣ የእግዚአብሔርን ጸጋና ረድኤት፣ ቀሚሱ ሰፊ ነውና ታጋሽነትን፣ ቻይነትን የሚያመለክት ሲኾን ውጭያዊው እይታ ደግሞ ለሥርዐት፣ ለሞገስና ለክብር እንዲሁም ከሌሎች የማኅበረሰብ ክፍሎች ለመለየት ነው::

[63]ይኽም ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዐርብ አይሁድ ሲሰቅሉት የእሾህ አክሊል የደፉበት መኾኑንና ስለ ሰው ልጆች ብሎ የደረሰበትን መከራ በማሰብ ንስሐ እንዲገቡ ብሎም በመከራው በመዳናቸውም ምስጋና እንዲያቀርቡ ለማሳሰብ ነው::

ከዚህ በኋላ ወንጌል ተነቦ ቅዱነታቸው እጃቸውን ታጥበው[64] ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ የተሾሙት ጳጳሳትም ተከትለው ገቡ።[65] ከዚህ ቀጥሎ መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉበት ሥርዐት ተፈጽሟል። ይኽንንም ለመፈጸም "ኪርያላይሶ" ተብሎ ከተጸለየ በኋላ ቅዱስ ፓትርያርኩ ጳጳሳቱን ወደ እርሳቸው ተራ በተራ ቀረብ በማድረግ "ንሣዕ መንፈሰ ቅዱሰ" በማለት "እፍ" አሉባቸው። ምእመናኑም "ይደልዎ፣ ይደልዎ፣ ይደልዎ" በማለትም ሥልጣነ ጵጵስናው የሚገባቸው መኾኑን መሰከሩ።

የክህነት አሰጣጥ ሥርዐቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የነበሩት በሙሉ ወደ ውጪ በመውጣት በዐውደ ምሕረቱ ላይ ተቀምጠው የቅዱስ ፓትርያርኩ በዐለ ሢመት ተከበረ። በበዐሉ ላይም በዐለ ሢመቱን የተመለከቱ ቅኔያት፣ መዝሙራት፣ ወረቦች እና ትምህርት ቀርቧል።

## ፯፥ ድኅረ ሥርዐተ ክዋኔ (reincorporation)

## ፯.፩. የዲቁና ሥልጣን ከተሰጠ በኋላ

ከዲቁና ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐት ጋር ተያይዞ ዲያቆኑንና ሥልጣኑን በተመለከተ ትኩረት የሚሰጥባቸው የተለያዩ ሥርዐቶች አሉ። አንድ ዲያቆን ከላይ በተጠቀሰው ኹኔታ ሥልጣነ ዲቁናን ከተቀበለ በኋላ ወዲያው ወደ አገልግሎት አይገባም። ቅዳሴ ለመቀደስና የተለያዩ ምልዓት ያላቸውን የዲቁና ተግባራት ለማከናወን ምሥጢር ማየት[66] አለበት። ምሥጢሩን የሚያየው ዲቁናውን እንደተቀበለ ወዲያው አይደለም። ምሥጢር ያላየና ሙሉ አገልግሎት ያልሰጠ "ንፍቅ ዲያቆን" ይባላል። ትርጒሙም ተጨማሪ፣ ረዳት ማለት ነው።[67]

በሥርዐተ ሢመቱ ላይ ዲያቆኑ የተሰጠውን ቀኖና (ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት… ሊኾን ይችላል) ፈፅሞ ከጨረሰ በኋላ ነው ምሥጢር ለማየት የሚበቃው።

---

[64] ንጹሕ የኾነ ከቁርባኑ ይቀበል። ንጹሕ ያልኾነ ግን አይቀበል። ለሰይጣንና ለመላእክተኞቹ በተዘጋጀ በመለኮት እሳት እንዳይቃጠል። በልቡናው ቂምን የያዘ ልዩ አሳብና ዝሙት ያለበት ቢኖር አይቅረብ።

[65] ወደ ውስጥ የገቡበት ምክንያት በውስጥ ኾነው ሥጋ ወደሙን መቀበል ስለሚገባቸው ነው። በዚያ ውስጥም የሜሮን አቀባብ ሥርዐት እንደሚፈጸም ገልጸውልኛል። የሚቀቡትም ራሳቸውን አምስት ቦታ ላይ ሲኾን የአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ምሳሌ ነው። አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ምሥጢረ ሥላሴ፣ ምሥጢረ ሥጋዌ፣ ምሥጢረ ቊርባን፣ ምሥጢረ ጥምቀትና ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ናቸው። እነዚህን ምሳሌ በማድረግ ሜሮኑን መቀባታቸው ምሥጢራቱን አምነው በመቀበል ለሕዝቡ ደግሞ በማስተማር ምሥጢራቱን መግለጽ ይችሉ ዘንድ ነው።

[66] ምሥጢር ማየት አንድ ዲያቆን ቤተ መቅደስ ገብቶ ማገልገል የሚችልባቸውን ንዋያተ ቅድሳትና አገልግሎታቸውን፣ የአገልግሎቱን ሒደት መረዳቱንና ለቅዱስ ቁርባን የውስጥ አገልግሎት መብቃቱን የሚያረጋግጥበት ሒደት ነው።

[67] ፍትሐ ነገሥት ዐንቀጽ ፳።

ምሥጢር ማየት የሚጀምረው ቤተ ልሔም[68] ውስጥ ካለው አገልግሎት ጀምሮ ነው። ቤተ ልሔም የሚሠራው ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በስተምሥራቅ አቅጣጫ ነው። ይኽ ሥጋ ወደሙ የሚዘጋጅበት ቤት "ቤተ ልሔም" የሚል ስያሜ የተሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው በቤተ ልሔም ከተማ በመኾኑ ነው። አንድም ቤተ ልሔም ትርጕሙም የእንጀራ ቤት[69] ማለት ስለኾነ የእርሱ ሥጋና ደም የሚዘጋጅበት ቤት በቤተልሔም ይመሰላል። ሌላም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን ያስገኘች (የወለደች) ቅድስት ድንግል ማርያም በመኾኗ ከእርስዋ የሕይወት እንጀራ ተገኝቷልና ቤተልሔም የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ነው ተብሎ ይታመናል። በቤተልሔም ምሥጢሩን ለዲያቆኑ የሚያሳዩት ቄሰ ገበዙ ወይም እና ሊቀ ዲያቆኑ ናቸው።

ዲያቆኑም ምሥጢራትን ካየ በኋላ ለማንም መንገር እንደሌለበት፣ በጥንቃቄና በንጽሕና ማገልገል እንደሚገባው ምክር አዘል ትምህርት ይሰጠዋል። ስለ አገልግሎቱ መነጋገር ያለበትም ምሥጢር ካዩት ዲያቆናት ጋር ነው። ምሥጢሩን ሳይጠብቅ የእግዚአብሔርን ክብር አጉድሎ ቢገኝ እንደ ዳታንና አቤሮን[70] እንደ ኤሊ ልጆች (እንደ አፍኒንና ፊንሐስ)[71] የእግዚአብሔር ቁጣና መቅሰፍት እንደሚወርድበት ቄሰ ገበዙና ሊቀ ዲያቆኑ አበክረው ይነግሩታል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ምሥጢሩን ጠብቆ ይኖራል። ምሥጢሩን እንዳየ ከካህናት
ጋር አብሮ መሶበ ወርቁን አክብሮ ወደ ቤተ መቅደስ ይሔዳል። መሶበ ወርቁን አክብረው ወደ ቤተ መቅደስ ለመሔድ ሦስት ካህናት ያስፈልጋሉ። አንደኛው ዲያቆን ከፊት ለፊት ኾኖ ቃጭል የሚመታ[72] ኹለተኛው ደግሞ መሶበ ወርቁን የሚያከብር (የሚሸከም) ሦስተኛው ቄስ ደግሞ ጽንሐሕ ይዞ የሚያጥን ነው።

በዚህ ኹኔታ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ ምሥጢር ያየው ዲያቆን ልብሰ ተክህኖ

---

[68] ቤተልሔም የቁርባን ኅብስት የሚጋገርበት፣ ከቤተ ክርስቲያን በምሥራቅ በኩል የሚሠራ ቤተልሔም ወይም ደጀ ብርሃን ማለት ነው። ተሰማ ሀብተ ሚካኤል። ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ፳፻፫፣ ገጽ ፫፻፳፱።

[69] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ፩፱፻፺፪፣ ገጽ ፩፻፲

[70] ዘዳ.፩፩÷፯

[71] ፩ሳሙ.፬÷፩፩

[72] የቃጭሉ ድምጽ የቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅን ድምፀ ቃለ ትምህርት ይወክላል። የቃጭል ድምፁ የማሰማቱ ምሥጢራዊ ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ ማቴ ፫፥ ፫፣ ሉቃ ፫፥ ፫-፬ "የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ ጥርጊያውን አቅኑ" ተብሎ የተጠቀሰውን የቅዱስ ዮሐንስን ስብከት የሚዘክር ነው። ከዮሐንስ ቀጥሎ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ወደ ዐለም መምጣቱንና ማስተማሩን ለማመልከት መሶበ ወርቁን ያከበረው ዲያቆን የቃጭሉን ድምፅ ተከትሎ ወደ ቤተ መቅደስ ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ የቃጭሉ ድምፅ አማንያንን ማንቂያ ነው። ይኽም በቤተ ክርስትያኑ ውስጥና ውጭ የተሰበሰበው ሕዝበ ክርስቲያን ቅዳሴውን በድምፅና በነቃ ሕሊና እንዲሳተፍና በጥንቃቄ ጸሎት እንዲያደርግ ለማንቃት ነው።

ለብሶ ከኾነ ያንኑ እንደለበሰ፣ ነጠላ ለብሶ ከኾነ ግን መስቀለኛ አጣፍቶ መልበስ አለበት። ይኸም የኾነበት ምክንያት የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ወገቡን ታጥቆ ወይም አደግድጎ ወደ ቤተ መቅደስ ይግባ ብሎ ስለሚያዝ ነው። ይኽ የማይገደፍ ሁልጊዜ ተግባራዊ መኾን ያለበት ሕግና ሥርዐት ነው። ዲያቆኑ ሥርዐተ ቅዳሴውን ተከታትሎ ከፈጸመ በኋላ ይቆርባል። ከምእመኑ ተለይቶ የክህነት ሥልጣን ስለተሰጠው የሚቆርበው ቤተ መቅደስ ውስጥ ኾኖ ነው እንጂ ምእመናኑ የሚቆርቡበት ቦታ ላይ ኾኖ አይደለም። ከዚህ በኋላ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ያሉት ሌሎች ምሥጢራት ይነገሩታል። እስከ ሦስት ቀን ድረስ እየገባ ሌሎች ሥርዐቶችን ኹሉ በጥንቃቄ እንዲያይ ይደረጋል። ለሦስት ቀንም እንዲቆርብ[73] ከተደረገ በኋላ ቤተ መቅደስ ውስጥ እንዲገባና እንዲያገለግል ይፈቀድለታል። ከዚህም በኋላ መስቀል ይዞ ዋና ዲያቆን ኾኖ መቀደስ ይችላል። በፊት ተከታይ (ንፍቅ) የነበረው ዲያቆን አሁን ዋና ዲያቆን (ሠራኢ ዲያቆን) ይኾናል ማለት ነው። ሠራኢ ከኾነ በኋላ ራሱን ችሎ መቀደስ፣ ማወደስ፣ ደሙን ማቀበል ይችላል። አገልግሎቱ በተግባር ታይቶለት ምሥጢሩን አይቷልና በቅዳሴው ሥርዐት ሙሉ አገልግሎት መስጠት ይችላል። የዲያቆን ሥራ ለቀሳውስት፣ ለጳጳሳትና ለምእመናን አገልግሎት መስጠት፣ መላላክ … ነው።

ይኽ ሲባል ግን በቤተ መቅደስ ውስጥ ያሉ ማንኛቸውንም ተግባራት የማከናወን ሥልጣን አለው ማለት አይደለም። በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዳይፈጸሙ የተከለከሉ የተለያዩ ድርጊቶች አሉ። እነሱም ታቦት (መንበሩን) መንካትና መዳሠሥ፣ ከመንበሩ ላይ ጢፍም ኾነ እጣን ማስቀመጥና ማንሣት አይችልም። ጥናውን ወገቡ ላይ ይዞ ፍም ያመጣል እንጂ ጫፉን ይዞ አያጥንም። እጣንም
ወደ ጥናው ውስጥ መጨመር አይችልም። እነዚህ የቅስና ሥልጣን ተግባሮች ናቸው። በዚህ ኹኔታ የቅስና ሥልጣን እስኪሰጠው ድረስ በእነዚህ አገልግሎቶች ፀንቶ ይቆያል።[74]

ዲያቆናት ሥልጣነ ክህነትን ከተቀበሉ በኋላ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ልማዳዊ አኗኗር እንደ ማንኛውም ግለሰብ በራስ ፈቃድና ምኞት ተጉዘው የፈለጉትን ማድረግ የማድረግ ሳይኾን በሕግና በሥርዐት ተወስኖ የመኖር ነው። ይኽንን ካላደረጉ ከክህነታቸው ይሻራሉ።[75]

[73]ሦስት ቀን እንዲቆርብ የሚደረግበት ምክንያት የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስን ሦስትነት ምሳሌን ለማመልከት ነው።

[74] ፍትሐ ነገሥት ዐንቀጽ ፰።

[75]ፍትሐ ነገሥት ዐንቀጽ ፯። ዲያቆናት ከማኅበረሰቡ ተለይተው የሚታዩበት ገጽታቸውን ለማመልከት ዲያቆን ዮሐንስና ዲያቆን ጽጌ ከራሳቸው የአኗኗር ልማድ በመነሣት የገለጹልኝ ጉዳዮች በአጠቃላይ የሚከተለውን ይመስላል። እነዚህም ጭፈራ ቤት አለመሔድ፣ ከሴት ጋር አለመገናኘት (ዝሙት አለመፈፀም)፣ አለመስከር፣ ትሑትና ታጋሽ መኾን፣ አለመጣላት፣ አልባሌ ቦታ አለመገኘትና ሌሎችም

## ፫.፪. የቅስና ሥልጣን ከተሰጠ በኋላ

የቅስና ሥልጣን ከተሰጠ በኋላ ኤጲስ ቆጶሱ ሥልጣኑን ለተቀበለው ካህን "... ከዚህ ቀን ጀምሮ ቅስና ተቀብሏል" በማለት የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣሉ። የምስክር ወረቀቱን እንደተቀበለ ግን አገልግሎት ይጀምራል ማለት ሳይሆን እስከ አርባ ቀን ድረስ[76] በቤተ ክርስቲያኗ ቀኖና መሠረት እንዲጾም፣ እንዲጸልይና እንዲሰግድ ይታዘዛል። ይኽን እንዳጠናቀቀ ሕዝበ ክርስቲያኑን የሚባርክበት የእጅ መስቀል በማምጣት በመንበሩ ላይ ለሰባት፣ ለዐሥራ ዐራት ወይም ለሃያ አንድ ቀናት እንዲጸለይበትና እንዲቀደስበት ያደርጋል። ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ የእነዚህ ቊጥሮች ትርጓሜ በሰባት ቤት የተወሰነበት ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ሥርዐት አንድ ሱባኤ ሰባት ቀናት፣ ኹለት ሱባኤ ዐሥራ ዐራት ቀናት ሲኾን ሦስት ሱባኤ ማለት ደግሞ ሃያ አንድ ቀናት[77] ማለት በመኾኑ እንደኾነ ተናግረዋል።

ቀሳውስት ቃለ እግዚአብሔርን የሚስተምሩ፣ የሚመክሩ፣ የጌታ ሐዋርያት፣ የኤጲስ ቆጶስ አማካሪዎች ናቸው ተብሎ በመጽሐፈ ዲድስቅልያ እንደተነገረው[78] ካህናት የአገልግሎት ሥራቸውን ሲጀምሩ በአለባበስ፣ በአነጋገር፣ በአካሄድ፣ በአጠቃላይ በአኗኗር ዘይቤያቸው ኹሉ ክህነታቸውን መጠበቅ ይገባቸዋል። ሕይወታቸውም በጥንቃቄ የተሞላ ሊኾን ይገባዋል። በአኗኗር ልማዳቸው ከሌላው ማኅበረሰብ እንዲለዩ የሚያደርጋቸው ሀገረ ሰባዊ የክህነት አለባበስ ሥርዐታቸው ነው። ቁርጭምጭሚታቸው ድረስ የሚደርስ ቀሚስ[79] ይለብሳሉ፤ በላዩ ላይ ነጠላ/ኩታ ይደርባሉ፤ ጥምጥም ወይም ቆብ[80] ጭንቅላቸው ላይ

በማኅበረሰባችን ዘንድ በጥሩ ሥነ ምግባር ውስጥ በማይካተቱ ጉዳዮች ላይ አለመሳተፍ ናቸው። በአንጻሩ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ፣ የባህልና ወግ መገለጫዎች የኾኑን ለምሳሌ ለታላላቆች አክብሮት መስጠት፣ መጠያየቅ፣ መከባበር፣ መረዳዳት፣ መቻቻል፣ ትምህርታቸውን በአግባቡ መከታተል አዘውትረው የሚተገብሯቸው ናቸው። ዲያቆናት በጭፈራ ቤት ተገኝተው ቢጠጡ፣ ቢሰክሩና ክህነታቸውን አቅለው ቢገኙ እንኳን በእግዚአብሔር ዘንድ በማኅበረሰቡ ዘንድም ነውር መኾኑን ገልጸዋል።

[76]ቀኖናው በዐርባ ቀናት እንዲወሰን የተደረገበት ምክንያት እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዐርባ ቀንና ሌሊት በገዳመ ቆሮንቶስ ጾሞ መጸለዩንና ዐርባ ጊዜ መገረፉን ለማስታወስ ነው።

[77]ቀናቱ ሰባት መኾናቸው ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለማጠየቅ ነው። እንደዚሁም መጽሐፍ ቅዱስ ጥበብ ቤቷን ሠራች ሰባት ምሰሶዎችንም አቆመች በማለት ሲገልጽ ጥበብ የኢየሱስ ክርስቶስ፣ ቤት የቤተ ክርስቲያን፣ ምሰሶ የተባሉት ደግሞ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌዎች ናቸው። ይኽም ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ሲመሠርት እነዚህን ምሥጢራት ያካተተ መኾኑን የሚያመለክት ነው ሲሉ ሊቀ

[78]*መጽሐፈ ዲድስቅልያ ዘአበዊነ ሐዋርያት*። (አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ ፳፻፬)፣ ዐንቀጽ ፲፮ ቊጥር ፴፩።

[79]አብዛኛውን ጊዜ የሚለብሱት ቀሚስ ጥቁር ቀለም ያለው ሲኾን አልፎ አልፎ ደግሞ ነጭ ይለብሳሉ። ቀሚሱ የሥጋንና የነፍስን ንጽሕና የሚያመለክት ሲኾን ጥቁሩ የሐዘን ምሳሌ ኾኖ ክርስቶስ የተቀበለውን መከራ ለማሰብ ነው። ነጭ ሲለብሱ ደግሞ ዘመነ ፍሥሐ ማለትም በትንሣኤና በተለያዩ ክብረ በዐላት ጊዜ ደስ መሰኘታቸውን ለመግለጽ ነው።

[80]አሁን አሁን ቀሳውስት ቆብ ማድረግ ጀምረዋል። ነገር ግን ቆባቸው ከመነኮሳት ቆብ የተለየ ነው። ይኽም የካህናት ቆብ መሐሉ ክፍት

ያደርጋሉ እንዲሁም የእጅ መስቀል ይይዛሉ።

ካህናት በማኅበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትና ከበሬታ አላቸው። ምክንያቱም "ካህን ሲያዩት ሰው ይመስላል፤ ፀበል ሲያዩት ውኃ ይመስላል" ተብሎ እንደተነገረው አገልግሎታቸው የነፍስና የሥጋ ደኅንነትን የሚያስጥና ከእግዚአብሔር የሚያገናኝ፣ የማሰርና የመፍታት ሰማያዊ ሥልጣን ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው በመኾኑ ነው።

ካህናት የክህነትን ሥልጣን ከተቀበሉ በኋላ ከምእምናን ጋር የሚያደርጉት የርስ በርስ ግንኙነት ቀድሞ ከነበረው ይለያል። ለምሳሌ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ መስቀል ያሳልማሉ (በመስቀል ይባርካሉ) እንጂ እንደሌላው ሰው እጅ አይጨብጡም። ይኽ የሰላምታ ልውውጥ የሚከናወነው ምእምናኑም ወደ ካህኑ በመቅረብ "ይፍቱኝ" ወይም "አሳልሙኝ" ሲሉ ካህኑ እግዚአብሔር ይፍታህ/ሽ/ በማለት በመስቀል ይባርካሉ። ምእመናኑ ካህናቱን መንገድ ላይም ኾነ ሌላ ቦታ ሲያገኙ ለመባረክ ወደ እነርሱ የሚሄዱት እግዚአብሔር ይፍታሽ/ህ/ መባልን ስለሚፈልጉና ባርኮቱ ከክፉ ነገር ይጠብቀናል ብለው ስለሚያምኑ ነው። ምእመናኑ በዓለም ውስጥ ሲኖሩ የተለያዩ ክፉ ድርጊቶችን ሊያከናውኑ ይችላሉና ወደ ካህናቱ ሄደው ሲባረኩም በውስጣቸው ያለ ስሜት "ዐውቄም ኾነ ሳላውቅ የሠራሁትን ኃጢአት ይቅር ይበሉኝ" የሚል ኑዛዜን ያዘለ ነው።

ካህናት ዲያቆናትንም ያሳልማሉ። ሲያሳልሙም "በረከተ እስጢፋኖስ (በረከተ ጳውሎስ) ይኅድር በላዕሌከ" እያሉ ነው። ካህን ሲያሳልሙ ወይም ርስ በርሳቸው ቡራኬ ሲሰጣጡ ሥልጣነ ክህነት በመቀበል የሚቀድመው ወይም በትምህርት ደረጃው ላቅ ያለው ካህን ቅድሚያ ያሳልማል። መጀመርያ የሚያሳልመው ካህን ሌላውን ተሳላሚ ካህን "ሢመተ እዴሁ ለቅዱስ ጴጥሮስ ይኅድር በላዕሌከ" ሲል ሌላኛው ካህን "ይፍቱኝ" ይላል። "ይፍቱኝ" ሲል አሳላሚው ካህንም ወዲያውኑ "እግዚአብሔር ይሲምከ ውስተ ዘለዓለም መንግሥቱ፤ እግዚአብሔር ይፍታሕ" ይለዋል።

ካህናት ሥልጣነ ክህነትን ከተቀበሉ በኋላ የሕዝበ ክርስቲያኑን ሥነ ምግባር በመቆጣጠር ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። ይኽን ተግባር የሚፈጽሙት የመቆጣጠርና የመምራት ሓላፊነትን ከእግዚአብሔር ስለተቀበሉ ነው። ይኽን ሲያደርጉም ባህላቸውንና ወጋቸውን ጠብቀው ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ

---

ሲኾን የመነኩሴዎች ደግሞ ድፍን ነው፡፡ ይኽ መኾኑ ማዕረጋቸውን ለመለየት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የካህናት መሐሉ ክፍት መኾኑ በትዳር ዐለም ውስጥ ያሉ መኾናቸውን ሲያመለክት የመነኩሴዎች ድፍን መኾኑ ደግሞ ድንግልናቸውን ለማመልከት ነው ሲሉ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ ገልጸውልኛል፡፡ እንዲሁም ያገቡ ካህናት ካላገቡት የሚለዩት ሱሪና ካፖርት በላዩ ላይ ደግሞ ነጠላ ደርበው በመልበሳቸውና ሻሽ በመጠምጠማቸው ነው፡፡

ይችሉ ዘንድ ዘወትር በማሳሰብ ነው። ለምሳሌ በአለባበስ፣ በአካሄድ፣ በአነጋገርና በሌሎችም የሀገርን ትውፊትና ልማድ በመጠበቅ ረገድ ትክክለኛ ሥርዐቶች ናቸው ብለው የሚያምኑባቸውን ለማስፈጸም ጥረት ያደርጋሉ። እነዚህን አለመፈጸም እግዚአብሔር የማይከብርባቸው መንገዶች ናቸው ብለው ስለሚያምኑ በረከትን እንደሚያሳጣና የእግዚአብሔር ቁጣ ሊነሣ እንደሚችል ይናገራሉ።

በሌሎችም ማኅበራዊ ጉዳዮች ለምሳሌ የተጣሉትን በማስታረቅ፣ የበደሉትን ይቅር በማለት፣ ንስሐ በመስጠት ዳግመኛ ወደ ጥፋት እንዳይገቡ በመምከር፣ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ (ማቴ ፰፥፩-፬)፣ (ሉቃ ፭፥፲፪-፲፯)፣ (ማር ፩፥፵-፵፭) ኢየሱስ ክርስቶስ ለምጻሙን ከለምጹ እንዲነጻ ካደረገው በኋላ ወደ ካህን ዘንድ በመሔድ ራሱን እንዲያሳይ አዞታል። ራስን ለካህን ማሳየት ኃጢአትን መናዘዝና ንስሐን መቀበል ነውና ቀሳውስት የንስሐ ልጅ በመያዝ ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲጠነክሩ በማድረግ፣ ሰው ሲሞት ኑዛዜን በመቀበልና ኑዛዜያቸው ተፈጻሚነትን እንዲያገኝ በማድረግ የሀገራችንን የአኗኗር ልማድ ገጽታ በጉልህ አንጸባርቀው ያሳያሉ። ካህናት ክህነታቸው እንዳይፈርስ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። አንድ ሚስት ብቻ እንድትኖራቸውም ይፈቀዳል። አጋጣሚ ባለቤታቸው በሞት ብትለይ ልክ በሞቱ በዐርባኛው ቀን መመንኮስ ይኖርባቸዋል። ሳይመነኲሱ ቀርተው ሌላ ሚስት ቢያገቡ ክህነታቸው ይፈርሳል።

## ፭.፫. የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ከተሰጠ በኋላ

ካህናት የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ከተቀበሉ በኋላ ሦስት ሱባኤ (ሦስት ሳምንታት ወይም ሃያ አንድ ቀናት) ይጾማሉ። ዘወትር ጤነኛ ይኾኑ ዘንድ ዕለት ዕለት ሥጋ ወደሙን መቀበል አለባቸው። ጳጳሳት ደናግል ናቸው።[81] ከሴት ጋር ተገናኝተው እንዳይሳሳቱ ምግባቸውን አዘጋጅቶ የሚቀልባቸው ወንድ መነኲሴ ሲኾን የላመ የጣመ መመገብ አልተፈቀደላቸውም። በሥርዐተ ክዋኔው ላይ የገቡትን ቃል ኪዳን አንድ በአንድ መፈጸምና የተሰጣቸውን ጸጋ መጠበቅ ይገባቸዋል። እነርሱ የሕዝበ ክርስቲያን መሪዎች በመኾናቸው ሃይማኖት እንዳይጠፋ ሕዝቡ እንዳይሳሳት መልካም እረኛ በመኾን ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቃሉ። ኤጲስ ቆጶስነት ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ስለኾነ ለዘመድ በውርስነት እንደማይሰጥ ፍትሐ ነገሥት ዐንቀጽ ፭ ቍጥር ፻፰፬ ይገልጻል።[82]

ሥልጣናቸውን ከእግዚአብሔር የተቀበሉና በክርስቶስ መንበር የሚያስተምሩ በመኾናቸውም መጠሪያቸውም "ኖሎት" (ጠባቂ) ነው። አኗኗራቸው ሰማያዊ

[81] መጽሐፈ ዲድስቅልያ ዘአበዊነ ሐዋርያት። (ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ ፳፻፬)፣ ዐንቀጽ ፳፫።

[82] ፍትሐ ነገሥት ዐንቀጽ ፭።

እንጂ ምድራዊ መምሰል የለበትም። በመኾኑም ቤት፣ መሬት፣ ንብረት፣ ሚስት፣ ልጅ፣ ርስት… ሳይሉ በቤተ ክርስትያን መኖር እንዳለባቸው በፍትሐ ነገሥት ዐንቀጽ ፭ እና መጽሐፈ ዲድስቅልያ ዘአበዊነ ሐዋርያት (፳፪፬) ዐንቀጽ ፴፰ ላይ ተገልጧል። ይኽንን ሥርዐት ሐዋርያት የመሠረቱበት ምክንያት ጳጳሳቱ በሀገሪቱ እንደልብ ተዘዋውረው ማስተማር፣ በአንድ ልብ ኾነው እግዚአብሔርን ማገልገል እንዲችሉ ነው።

## ፯. ማጠቃለያ

የክህነት ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔ አፈጻጸም ትውፊትን መሠረት ያደረገ ሲኾን አመጣጡም የሐዲስ ኪዳን መሥራች ከኾነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጀምሮ እስከ ሐዋርያት፣ ከሐዋርያት ደግሞ ሰባቱ ዲያቆናት ከሰባቱ ዲያቆናት እንዲሁ ሰባ አርድእት ከዚያም ሌሎች አባቶች ሲፈጽሙበት የነበረውን ሥርዐት ተከትሎ ነው። በሥርዐተ ክዋኔው ወቅት የሚፈጸሙ ድርጊቶች፣ ለአገልግሎት የሚውሉ ቁሶች፣ ንግግሮች፣ ጸሎቶች ኹሉ ሃይማኖትን ትውፊትንና ልማድን የሚያንፀባርቁ ገጽታዎች ናቸው። ጥንት የሃይማኖቱ ተከታዮች ሲፈጽሙት የነበረው የክህነት አሰጣጥ ሥርዐት የክርስትናን ምሥጢር እንዲገልጹ ኾነው የተደነገጉ፣ ክርስቶስን ለመከተል የሚያስችሉ ገጽታዎችን በማንፀባረቅ ሲኾን ሥርዐቱ ትርጕም ይኖረው ዘንድ የማኅበረሰቡን ልማድና ዕውቀት በመመርኮዝ ነው። ይኽም ማለት ካህኑ እየኖረበት ያለውን ማኅበረሰብ ዕውቀት ግምት ውስጥ በማስገባት እንደ አመለካከታቸው፣ የአኗኗር ዘይቤያቸውና ስልታቸው የክርስትና

ትምህርት በመስጠት ሕዝቡን በጥሩ ሥነ ምግባር ማነጽ ሃይማኖታዊ እሴቶችን በማስጠበቅ ለዘላለማዊ ሕይወት ማብቃት ማለት ነው።

በመኾኑም ሥልጣነ ክህነትን የተቀበለ ግለሰብ ማስታረቅ፣ ማማለድ፣ ችግር መፍታት፣ የተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮችን መምራትና ማደራጀት በአጠቃላይ በነፍስም ኾነ በሥጋ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን መስጠት ይጠበቅበታል። የክህነት ሕይወት ከከፍተኛው የመንፈሳዊ አገልግሎት ጎን ለጎን ማኅበራዊና ግለሰባዊ የኾኑ ተግባሮችም የሚከናወኑበት ነው። ሦስቱ የሥልጣነ ክህነት ዐይነቶች በየደረጃቸው የቤተ ክርስቲያን ሥርዐትና አምልኮ ለመፈጸም ወሳኝ ናቸው። አገልግሎታቸውም በመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዝ መሠረት በፍትሐ ነገሥትና በመጽሐፈ ዲድስቅልያ እንደተገለጸው በሦስት ወገን ተከፍሎ የሚታይ ነው። እነርሱም ትምህርተ ወንጌልን ማስተማር (ማቴ ፳፰÷፲፱-፳)፣ የሕዝቡን ኃጢአት

ማስተስረይ፣ (ዮሐ ፳፥፳፫)፣ (፩ኛ ጴጥ ፩÷፲፯) እና ምእመናንን መጠበቅ (ዮሐ ፳፩÷፲፭-፲፯) ናቸው። እነዚህ የክህነት ዓይነቶች የሚሰጡትም እንደ ብሉይ ኪዳን ሥርዐት ለአንድ ወገን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጸጋና ካህናት ለመረጡት ለየትኛውም ሰው ነው። ይኽ ሲባል ግን ኹሉም ተነሥቶ ክህነትን መቀበል እፈልጋለሁ ቢል ሥርዐተ ክዋኔው የሚፈጸምለት ሳይኾን በየደረጃው አስፈላጊውን መስፈርት ማሟላቱ ታይቶ ነው። በመኾኑም ለዚህ ወግ መዓርግ ለመብቃት ሦስት ደረጃዎችን ማለትም መለየት (separation)፣ ሽግግር (transition)፣ እና መመለስ (reincorporation) የተሰኙ ደረጃዎችን ማለፍ አለበት።

## ፮.፩. የጥናቱ ግኝቶች

ሀ. ሥልጣነ ክህነትን መቀበል ከዝቅተኛው ማኅበረሰባዊ ቦታ ወደ ከፍተኛው የሚያሸጋግር በመኾኑና ሥልጣኑን ለመቀበል ሥርዐት የተበጀለት በመኾኑ ወግ መዓርግ ነው። የሥልጣነ ክህነቱ አሰጣጥ ትውፊታዊ መርኆዎችን የያዘ በመኾኑም ሀገረ ሰባዊ ልማድ ተብሎ ሊጠራ የሚችል ሥርዓትን የተከተለ ነው።

ለ. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የክህነት ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔ የሚፈጸመው ለዲቁና፣ ለቅስናና ለኤጲስ ቆጶስነት መዓርጋት ብቻ ነው።

ሐ. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሁን ያለው የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዐት መመሪያ መሠረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ክህነትን የሰጠበት ሥርዐት ነው። ሥርዐቱ ሰዎች ምሥጢራትንና ሥርዓተ አምልኮትን በቤተ ክርስቲያን ለመፈጸም የሚችሉበትን ኃይል እንዲያገኙ የሚያስችል ሲኾን ቤተ ክርስቲያን የተባለውን ተቋም ለመመሥረትም እነዚህ ካህናት የግድ መኖር አለባቸው።

መ. የዲቁና፣ የቅስናና የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔዎች ተመሳሳይነትና ልዩነት አላቸው።

## ተመሳስሎ

- በሦስቱም ደረጃዎች ካህናት ሥልጣነ ክህነትን ከመቀበላቸው በፊት የሚፈጽሟቸው የተለያዩ ቅድመ ሥርዐተ ክህነት ሥርዐቶች አሏቸው።

- የሦስቱም ሥርዐተ ክዋኔ በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ይከናወናል፡፡
- በሦስቱም ሥርዐተ ክዋኔዎች ላይ የአንብሮተ ዕድ (እጅ መጫን) እና የጸሎት ሥርዐት ይካሄዳል፡፡
- በሦስቱም ሥርዐተ ክዋኔዎች ላይ ሥልጣኑን የተቀበሉ ካህናት ለተከታታይ ቀናት ይቆርባሉ (የመቁረቢያው ቀን ቁጥር ቢለያይም)፡፡

## ልዩነት

በዲቁናና በቅስና ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔዎች ሥልጣን የሚሰጠው በአንድ ሊቀ ጳጳስ ነው፡፡ ለሥርዐቱ ሕዝብ እንዲሰበሰብ አይደረግም፤ መርሐ ግብር አይወጣለትም፡፡ በሰጪውና በተቀባዩ ስምምነት ብቻ የመስጪያው ቀን ይወሰናል፡፡ በኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን አሠጣጥ ሥርዐተ ክዋኔ ግን መርሐ ግብሩ ለሕዝብ ይፋ ኾኖ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ምእመናን፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትና የሃይማኖት መሪዎች በተገኙበት ይፈጸማል፡፡ ሥርዐቱ የሚፈጸመው ከኹለት በላይ በኾኑ ሊቃነ ጳጳሳትና በፓትርያርክ ነው፡፡

- የኤጲስ ቆጶስነት ሥልጣን ከቅስናና ዲቁና ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐት የሚለየው በአስኬማ፣ በልብሰ ተክህኖ አለባበስ፣ በአርዌ ብርት አሰጣጥ፣ በስም አወጣጥና ቃል ኪዳን በመግባት የሚከናወን በመኾኑ ነው፡፡ እንዲሁም የቅስና ሥልጣን ከዲቁና ሥልጣን አሰጣጥ ሥርዐት የሚለየው በንፍኀት፣ የቀሳውስት አንብሮተ እድ ወይም ዳሠሣ ሥርዐት የሚፈጸም በመኾኑ ነው፡፡
- ሥልጣነ ክህነቱ ሲሰጥ ለሦስቱም የክህነት ደረጃዎች የሚጸለየው ጸሎት የተለያየ ነው፡፡ ሦስቱም ዐይነት ጸሎቶች የእያንዳንዱን ክህነት ዐይነትለመስጠት
- የሚያስችል ይዘትና ሊፈጽሙ የሚገባቸውን ተግባራት የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ሠ. የክህነትን ሥልጣን ለመቀበል መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

ለዲቁና ➔ ድንግልና፣ ጥሩ ሥነ ምግባርና የክህነት ትምህርት

ለቅስና ➔ ዲቁና፣ ትዳር መያዝ ወይም ምንኩስናና ጥሩ ሥነ ምግባር

ለኤጲስ ቆጶስነት ➔ ድንግልና፣ ጥሩ ሥነ ምግባር፣ ዲቁና፣ ቅስና፣ የአስተዳደር ብቃትና ምንኩስና ወይም ቁምስና ናቸው፡፡

ረ. ካህናት ሥልጣነ ክህነቱን ከተቀበሉ በኋላ በአለባበስ፣ በአነጋገር፣ በአኗኗር

ዘይቤ፣ ከሌላው ማኅበረሰብ የተለየ የአኗኗር ልማድ ያበጃሉ። እነዚህ የአኗኗር ልማዶቻቸው ሃይማኖታዊና ባህላዊ ገጽታዎችን የሚያንጸባርቁ ናቸው።

ሰ. ካህናት በሥርዐተ ክዋኔው ላይ በተቀበሉት ሥልጣን መንፈሳዊና ሥጋዊ፣ ማኅበረሰባዊና ግለሰባዊ አገልግሎት ይሰጣሉ። (የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዐተ ክዋኔ ካህናት አገልግሎትን መስጠት ይችሉ ዘንድ የሚያስችላቸውን ኃይል የሚሰጥ ነው።)